**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት**

**ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ**

**DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA**

**OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE**

2ኛ ዓመት ቁጥር 40
አርባምንጭ መጋቢት 5_qN 2'ሺ፲6 ›.M

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት
ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 40
Arbaminch March, 2024


## አዋጅ ቁጥር 43/2016

## የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ

በኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ ህገ-መንግሥት እና ኢትዮጵያ ፈርማ ባጸደቀቻቸው የዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች የተደነገገውን የዜጎች የመደራጀት መብት እና ከዚሁ መብት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች መብቶችን በተሟላ መልኩ ለማስከበርና ተግባራዊ ለማድረግ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የመንግሥት አሠራር በግልጽነት፣ በተጠያቂነትና በአሳታፊነት እንዲከናወን ለማድረግ የነቃና በነፃነት የተደራጀ ማሕበረሰብ ለመፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በማመን፤

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ተጠያቂነት እና የሕብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ድርጅቶቹ ሥራቸውን በሕግ መሠረት መሥራታቸውን ቁጥጥር ማድረግ በማስፈለጉ፤

ዘርፉ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚሰጠውን ፋይዳ በመረዳት

## PROCLAMATION No. 43 /2024

## SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE CIVIL SOCIETIES ORGINAZATION PROCLAMATION.

**WHEREAS,** it is found necessary to enact a law so as to give full effect to the freedom of association and other related rights as enshrined in the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia , South Ethiopia Regional State and as per the International Human Rights Instruments ratified by Ethiopia;

**FIRMLY CONVINCED,** that the existence of an active and freely organized society is imperative to ensure that government activity is transparent, accountable and participatory ;

Recognizing, the need to regulate civil society organizations accountability and ensuring maximum public benefit from the sector;

በክልሉ ብቻ ወይም በፌዴራል ተመዝግበው በክልሉ ውስጥ ፕሮጀክት የሚተገብሩ ሁሉም ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በምዝገባ፣ በስምምነት እና ስምሪት ረገድ ምቹ አገልግሎት የሚያገኙበት እንዲሁም በተሻለ ሁኔታ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ወጥ የሆነ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ተስፋፍተው በክልሉ ልማትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ያላቸው ሚና እንዲጎለብት ለማድረግ የተመቻቸ ምህዳር መፍጠርና በሕብረተሰቡ ዘንድ የበጎ አድራጎት እና የበጎ ፈቃደኝነት ባሕል እንዲዳብር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በህገ-መንግስት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀፅ (3) በተሰጠዉ ሥልጣን መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት **"የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 43/2016"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) **"ክልል"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

**COGNIZANT OF,** the importance of this sector to the general public, it become necessary to provide better service and creating suitable conditions in registration, project agreement process and implimentation for both regionally and Federally registered civil societies organizations by enacting condusive law;

**WHEREAS** it is necessary to create an enabling environment for civil society organizations to expand and enhance their role in the development and democratic system building of the region, and to foster a culture of charity and volunteerism among the community;

**NOW THEREFORE,** South Ethiopia Regional State Council in accordance with the power given on Article 54(3) of the Regional Constitution issued this proclamation.

## SECTION ONE
## GENERAL PROVISIONS

**Short Title**

This Proclamation may be cited as the □Civil Societies Organizations Proclamation No. 43/2024□.

**2. Definition**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1) "**Region**□ means the South Ethiopia

| | |
|---|---|
| ነው፤ | Regional State; |
| 2) **“ባለስልጣን”** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ነዉ፤ | 2) □**Authority**□ means the Ethiopia Federal Democratic Republic Government Civil Society Organizations Authority; |
| 3) **“ፍትሕ ቢሮ”** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ፍትሕ ቢሮ ነው፤ | 3) □**Justice Bureau”** means the South Ethiopia Regional State Justice Bureau; |
| 4) **“ፋይናንስ ቢሮ”** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ፋይናንስ ቢሮ ነው፤ | 4) “**Finance Bureau**□ means the South Ethiopia Regional State Finance Bureau.; |
| 5) **“የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ወይም ድርጅት”** ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሠረት፣ የመንግሥት አካል ያልሆነ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት ያልወገነ እና ሕጋዊ ዓላማን ለማሳካት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አካል ሲሆን የሙያ ማኅበራትን፣ የብዙኀን ማህበራት እና የድርጅቶች ኅብረቶችን ይጨምራል፤ | 5) “**Organizations of Civil Societies**□ means hereafter called (Organization“) means a non-governmental, non□partisan entity established at least by two or more persons on a voluntary basis (Non profitable) and registered for lawful purpose, and includes non□governmentorganizations,professionl associations, mass based societies and consortiums , a foreign organizations or local organizations; |
| 6) **“ሀገር በቀል ድርጅት”** ማለት በክልሉ ውስጥ ሕጋዊ ሥራን ለመሥራት በዚህ ሕግ መሠረት በኢትዮጵያዊያን ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆኑ የውጭ አገር ዜጎች ወይም በሁለቱ አማካኝነት በጋራ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤ | 6) “**Local organization**” means a civil society organization formed under the laws of Ethiopia by Ethiopians, foreigners resident in Ethiopia or both; |
| 7) **“የውጭ ድርጅት”** ማለት በውጭ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋመና በኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው፤ | 7) “**A foreign organization**□ means a non-governmental organization formed under the laws of foreign countries and registered to operate in Ethiopia; |
| 8) **“የሙያ ማኅበር”** ማለት አንድን ሙያ መሠረት በማድረግ የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን ዓላማውም | 8) “**Professional association**□ means an organization formed based on a profession, and its objectives may include protecting the rights and interests of its members; |

| | |
|---|---|
| የአባላቱን መብትና ጥቅም ማስከበር፣ የሙያ ሥነ-ምግባርን ማሳደግ፣ የአባላትን አቅም መገንባት እንዲሁም በሙያቸው ለሕዝብና ለሀገር አስተዋጽዖ ማድረግን የሚጨምር ነው፤ | promoting professional conduct, building the capacities of members or mobilize professional contributions of its membership to the community and the country; |
| 9) **“ኅብረት”** ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ድርጅቶች የሚቋቋም ስብስብ ሲሆን የኅብረቶችን ህብረት ይጨምራል፤ | 9) “**Consortium**” means a grouping formed by two or more civil society organizations, and includes consortia of consortiums; |
| 10) **“የዘርፍ አስተዳዳሪ”** ማለት የተለየ ፈቃድ በሚያስፈልጋቸው የሥራ ዘርፎች ለሚሰማሩ ድርጅቶች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥ እና ተገቢውን ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ነው፤ | 10) “**Sector administrator**” means a regional government body located in every level mandated to issue licenses for organizations operating in sectors that require special licensing; |
| 11) **“ጉባዔ”** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የክልሉ ፋይናንስ እና የፍትሕ ቢሮ አካል ሆኖ ተቋቋመው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጉባዔ ነው፤ | 11) **“Council”** means the Council established as part of Justice Bureau and Finance Bureau in accordance with this proclamation; |
| 12) **“ልዩ ፈቃድ”** ማለት በአንድ ስራ ላይ ለመሰማራት በህግ ፈቃድ እንደሚያስፈልግ የተገለጸ በሆነ ጊዜ በዚህ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚሰጥ የፈቃድ አይነት ነው፤ | 12) “**Special License**” is a type of license given by sector adminstrators to participate in certain activities when prescribed by law; |
| 13) **“የራስ አስተዳደር”** ማለት ድርጅቶች በምክር ቤቱ አማካኝነት ራሳቸውን ለማስተዳደር በፈቃዳቸው በሚያወጡት የሥነ ምግባር ደንብ የሚመራ አስገዳጅ የቁጥጥር ሥርዓት ነው፤ | 13) “**Self-Regulation**” means a mandatory regulatory system led by a voluntary code of conduct adopted by Organizations through the Council to govern them; |
| 14) **“የሥራ አመራር አባላት”** ማለት ተጠሪነታቸው ለድርጅቱ የበላይ አካል ወይም እንደሁኔታው ለድርጅቱ ጠቅላላ ጉባዔ ወይም ቦርድ ሆኖ የድርጅቱን የሥራ ሂደት እንዲከታተሉና እንዲቆጣጠሩ በድርጅቱ | 14) “**Members of Management**” mean persons who are accountable to the higher body of the organizations (depending on its Article of association General Assembly or |

አባላት ወይም በድርጅቱ ቦርድ የተመረጡ ሰዎች ናቸው፤

15) **“የሥራ መሪ”** ማለት የድርጅቱን የዕለት ከዕለት ሥራ በበላይነት እንዲመራ በውል የተቀጠረና ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ለድርጅቱ ቦርድ የሆነ ግለሰብ ነው፤

16) **“ሰው”** ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው፤

17) በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ያካትታል።

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

1) ይህ አዋጅ በሚከተሉት ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡-

ሀ/ በክልሉ ተመዝግበው በሚንቀሳቀሱ ሀገር በቀል ድርጅቶች፣

ለ/ በባለስልጣኑ ተመዝግበው በክልሉ ውስጥ ፕሮጀክት በሚተገብሩ ድርጅቶች፣

2) ይህ አዋጅ በሚከተሉት ተቋማት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡-

ሀ/ በዕድር፣ ዕቁብና መሰል ባሕላዊ ስብስቦች፣

ለ/ በሃይማኖት ተቋማት፣

ሐ/ በሌላ ሕግ መሠረት በተቋቋሙ ተቋማት።

**ክፍል ሁለት**

**የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጉባዔ**

**4. መቋቋም**

የፋይናንስ ቢሮና የፍትሕ ቢሮ አካል የሆነ የሲቪል ማህበረሰብ

Board ) and elected to regulate affairs of organization by members or Council,

15) “**Officer**” means a person hired to manage the day to day operations of the organization and accountable to the management committee or Board of the organization;

16) “**Person**” shall mean any physical or juridical person;

17) Any expression in the Masculine gender refers the Feminine.

**3. Scope of Application**

1) This Proclamation shall be applicable on:

a/ Local Organizations registered and operating in the Region,

b/ Organizations registered by the Authority and operating projects in the Region.

2) This Proclamation shall not be applicable to:

a/“Edir“, “Equb“ and similar traditional institutions;

b/religious institutions; „

c/ Organizations estabilished under other laws.

**SECTION 2**

**COUNCIL OF CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS**

**4. Establishment**

The of Civil Society Organizations, which is a part

| | |
|---|---|
| ድርጅቶች ጉባዔ ከዚህ በኋላ "**ጉባዔ**" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቋሟል፡፡ | of the Finance Bureau and the Justice Bureau, hereinafter referred to as the "Council" has been established by this decree. |
| **5. የጉባዔ አባላት** | **5. Members of the Council** |
| 1) የጉባዔ አባላት በዘርፉ ልምድ ያላቸውን ተወካዮች ባካተተ መልኩ በሚከተለው ሁኔታ የሚሰየሙ ዘጠኝ አባላት ይኖሩታል፤ | 1) Members of the Council shall have nine members who shall be appointed in the following manner,including representatives with experience in the field; |
| ሀ/ በፋይናንስ ቢሮ እና በፍትሕ ቢሮ ኃላፊዎች አቅርቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሰየሙ የመንግስት መስሪያ ቤት ሁለት ተወካዮች፣ | a/ Two representatives of the government office to be appointed by the head of the state on the recommendation of the Finance Bureau and Justice Bureau officials. |
| ለ/ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች የሚሰየም አንድ ተወካይ፣ | b/ One representative to be appointed by the head of the regional government from among the sector adminstrators, |
| ሐ/ ከክልሉ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የሚሰየም 2 ተወካይ፣ | c/ Two representatives to be appointed from the Council of Civil Society Organizations of the region. |
| መ/ በሲቪል ማኅበረሰብ ሥራ ተገቢው ዕውቀትና ልምድ ያለውና በግል ብቃት በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰየም አንድ ባለሙያ፤ | d/ An expert who has the appropriate knowledge and experience in civil society work and is appointed by the head of government based on personal competence; |
| ሠ/ ከክልሉ ሁሉም አካል ጉዳተኞች ማህበራት ህብረት የሚሰየም አንድ አባል፤ | e/ One member to be appointed from the Federation of all Disabled Persons Associations of the region; |
| ረ/ ከክልሉ ወጣቶች ማህበራት ህብረት የሚሰየም አንድ አባል፤ | f/ One member to be appointed from the Federation of Youth Associations of the region; |
| ሰ/ ከክልሉ ሴቶች ማህበር የሚወከል አንድ አባል፡፡ | g/ One member representing the women's association of the region. |

2) የጉባዔው አባላት ከየትኛውም ዓይነት ተጽዕኖ ነፃ በመሆን ሥራቸውን በቅንነትና በታማኝነት ያከናውናሉ፤

3) የጉባዔ ሊቀመንበር በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) ከተጠቀሱት ዉስጥ የሚሰየም ሲሆን የሥራ ዘመኑም ሦስት ዓመት ይሆናል።

## 6. የጉባዔው ስልጣንና ተግባር

ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የመደራጀት መብትን አፈጻጸም በማጎልበትና በዘርፉ የሕብረትሰብ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ ረገድ ፋይናንስ ቢሮና ፍትሕ ቢሮ የሚመራባቸዉ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤

2) በፋይናስ ቢሮ እና በፍትሕ ቢሮ ኃላፊዎች በጋራ በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ይግባኞችን ይመረምራል፣ ውሳኔ ይሠጣል፤

3) ጉባዔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዩን የሚመረምር ገለልተኛ አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ይሰይማል፣ ኮሚቴው በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሠረትም አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል፤

4) የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴውን አሰራር የሚወስን መመሪያ ያወጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

5) በዚህ አዋጅ መሠረት በክልሉ የተመዘገቡ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን በተመለከተ ፋይናንስ ቢሮ እና ፍትሕ ቢሮ በቅንጅት የሚያወጣቸውን መመሪያዎችን መርምሮ ያጸድቃል፤

6) በፋይናንስ ቢሮ እና ፍትሕ ቢሮ የሚቀርቡለትን ሌሎች

2) The members of the Council shall carry out their work honestly and faithfully, free from any influence;

3) The Chairman of the Council shall be appointed by the head of state from among those mentioned in sub-Article 1 (a) of this Article and his term of office shall be three years.

## 6. Powers and functions of the Council

The Council shall have the following powers and functions:-

1) In enhancing the implementation of the right to association and ensuring the benefit of society in the sector, shall set policy directions leading the Finance Bureau and the Justice Bureau.

2) Investigates appeals submitted on the decisions made jointly by Finance Bureau and Justice Bureau heads, and gives a decision;

3) When the Council deems it necessary, it appoints an independent complaint investigation committee to investigate the matter, and makes an administrative decision based on the committee's proposal;

4) Issue Rules of procedure for the complaint investigation committee and follow up its implementation;;

5) Examines and approves the manuals issued jointly by the Finance Bureau and the Justice Bureau with respect to civil society organizations registered in the region according to this proclamation;

6) Investigate and decide other matters submitted to it by the Finance Bureau and the Justice Bureau.

| | |
|---|---|
| ጉዳዮችን መርምሮ ይወስናል። | |
| **7. የጉባዔው አሰራርና ስብሰባ ሥነ-ሥርዓት** | **7. The procedure and meeting procedure of the Council** |
| የጉባዔው የአሠራር ሥነ-ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፡- | The proceedings of the meeting shall be as follows: |
| 1) የጉባዔው ሊቀመንበር የጉባዔን ስብሰባ ይመራል፤ | 1) The Chairman of the Council presides over the meeting of the Council; |
| 2) ሊቀመንበሩ በማይገኝበት ጊዜ በስብሰባው የተገኙ አባላት ከመካከላቸው ስብሳቢውን ይሰይማሉ፤ | 2) In the absence of the chairman, the members present at the meeting shall appoint the chairman from among themselves; |
| 3) የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ እና ፍትሕ ቢሮ ኃላፊዎች ድምፅ የመስጠት መብት ሳይኖራቸዉ በጉባዔ ስብስባ ላይ ይሳተፋሉ፤ | 3) Heads of the Regional Finance Bureau and Justice Bureau participate in the Council meeting without having the right to vote; |
| 4) የጉባዔው መደበኛ ስብሰባ በየሶስት ወሩ የሚካሄድ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በማናቸውም ጊዜ የጉባዔው ሊቀመንበር ወይም በፋይናንስ ቢሮ ወይም ፍትሕ ቢሮ ሃላፊ ወይም ከጉባዔው አባላት አንድ ሶስተኛው ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፤ | 4) The regular meeting of the Council is held every three months, and if necessary, the chairman of the Council or the head of the finance Bureau or the head of the justice Bureau or one-third of the members of the Council may hold an extraordinary meeting at any time; |
| 5) በማንኛውም ስብሰባ አብላጫ የጉባዔው አባላት ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤ | 5) When the majority of the members of the Council are present at any meeting, it shall be a quorum; |
| 6) ማንኛውም ውሣኔ በስብሰባው በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፤ ሆኖም የጉባዔው ድምጽ እኩል ከሆነ ሊቀመንበሩ ያለበት ወገን ውሣኔ የጉባዔው ውሣኔ ይሆናል፤ | 6) Any decision shall be made by majority vote of the members present at the meeting; However, if the votes of the Council are equal, the decision of the party to which the chairman votes shall prevail. |
| 7) ጉባዔው በድምጽ ብልጫ በሚወሰንበት ጊዜ የአነስተኛው ድምጽ አስተያየት ከነምክንያቱ በስብሰባው ቃለ-ጉባዔ መመዝገብ አለበት፤ | 7) When the meeting is decided by a majority vote, the opinion of the minority vote shall be recorded in the minutes of the meeting; |
| 8) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል። | 8)Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may issue its own Rules of procedure for meetings. |

9) የጉባዔው አባላት በጉባዔው ስብሰባ ተገኝተው ሲሳተፉ ተመጣጣኝ አበል ይከፈላቸዋል። የክፍያዉም መጠን ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣዉ ድንብ ይወሰናል።

**8. የጉባዔው አባላት የሥራ ዘመን**

1) የጉባዔው አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሲሆን አባላቱ ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ፤

2) የሥራ ዘመኑ ከማለቁ በፊት መልቀቅ የሚፈልግ አባል ጥያቄውን ለጉባዔው በጽሑፍ በማቅረብና ጉባዔው ሲወስን መልቀቅ ይችላል።

**ክፍል ሶስት**

**የወል ሥልጣንና ተግባራት**

**9. የፋይናንስ ቢሮ እና ፍትሕ ቢሮ የወል ሥልጣንና ተግባራት**

የፋይናንስ ቢሮም ሆነ የፍትሕ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ኃላፊነቱን ለመወጣት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል፤

2) ድርጅቶች የክልሉ መንግሥት በሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና ሕጎች የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል፤

3) በዘርፉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ

9) Members of the Council shall be paid a reasonable perdiem, which shall be determined by the Regulation, when they attend and participate in the meeting of the Council.

**8. Term of office of the members of the Council**

1) The term of office of the members of the Council is three years and the members may be re-elected for one more term;

2) A member who wants to resign before the end of his term of office can resign by submitting his request in writing to the Council and when decided by the Council.

**SECTION THREE**

**COMMON POWERS AND FUNCTIONS**

**9. Common Powers and Functions of the Finance Bureau and the Justice Bureau**

Both the Finance Bureau and the Justice Bureau shall have the following powers and functions:

1) works in cooperation and coordination with the relevant bodies to fulfill its responsibilities;

2) Encourages organizations to actively participate in the policies and laws enacted by the regional government;

3) Shall cooperate with relevant government

መርዳትን ለመከላከል የሚያስችሉ ሥራዎችን ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

4) የድርጅቶችን ንብረት ማስተላለፍና ማስወገድን በተመለከተ አስፈላጊዉን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ ያስተላልፋል፤ ያስወግዳል፤እንዲተላለፍም ድጋፍ ያደርጋል፤

5) የበጎ ፈቃደኝነትን ባሕልና እንቅስቃሴ የማበረታታት ስራ ይሰራል፤

6) ድርጅቶች የሚያከናውኗቸውን የልማት ሥራዎች መንግሥት ከሚያወጣቸው የልማት ዕቅዶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ያግዛል፤

7) ድርጅቶች ሲመዘገቡና ሲሰማሩ የመረጃ ልውውጥ ማድረግና አያያዙን የማዘመን ሥራ ያከናውናል፤

**8)** ከፌዴራል መንግስትና ከአቻ ክልሎች እንዲሁም በክልሉ ዉስጥ ካሉ ከባለድርሻ አካላት እና ድርጅቶች ጋር ቋሚ የምክክር መድረኮችን ያዘጋጃሉ፤ ይመካክራሉ፡፡

**10. የፍትሕ ቢሮ ሥልጣንና ተግባራት**

የፍትሕ ቢሮው በሌላ ህግ የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ዉስጥ ብቻ ለሚሰማሩ ድርጅቶችን ይመዘግባል፣ፈቃድ ይሰጣል፣ ይደግፋል፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፤

2) ድርጅቶች ሥራቸውን በሕግ አግባብ እና በተመዘገቡበት ዓላማ መሰረት ማከናወናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤

bodies in the field to prevent the to prevent money loundering and legalization of property obtained through criminal activities and to prevent the financing of terrorism;

4) Shall carry out the necessary supervision and control regarding the transfer and disposal of assets of organizations; it shall transfer, dispose of, and support the transfer thereof;

5) Promotes the culture and activities of volunteerism;

6) Helps organizations to align their development activities with the development plans issued by the government;

7) It carries out the work of exchanging information and updating the records when organizations register and deploy;

8) Shall establish and consult with the Federal Government and the Regional States, as well as with stakeholders and organizations within the Region;

**10.Powers and functions of the Bureau of Justice**

Without prejudice to the powers and functions given by other laws, the Bureau of Justice shall have the following powers and functions;

1) Registers, licenses, supports and coordinates the work of organizations that operate only in the Region;

2) Shall Monitor, control and support whether

| | |
|---|---|
| | organizations carry out their work in accordance with the law and the purpose for which they are registered; |
| 3) የተመዘገቡ ድርጅቶችን ዓመታዊ የሥራና የገንዘብ እንቅስቃሴ ሪፖርት ላይ በዚህ ሕግ በተወሰነው መሠረት ይመረምራል፤ | 3) Examine the annual work and financial activities report of registered organizations as determined by this Proclamation; |
| 4) ድርጅቶች ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የውስጥ አስተዳደር እና የራስ አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤ | 4) Provides the necessary support for organizations to have an internal management and self-admnstration system that ensures transparency and accountability, and monitors its implementation; |
| 5) ድርጅቶች በሀገሪቱና በክልሉ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ፣ ሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ እና የልማት እንቅስቃሴ ያላቸውን ሚና አስመልክቶ ተገቢውን ጥናት ያካሂዳል፤ የክልሉን መንግሥት ያማክራል፤ | 5) Conducts appropriate research on the role of organizations in building a democratic system, protection of human rights and development activities in the country and the region; and consults the regional government; |
| 6) ይህንን አዋጅ መነሻ አድርጎ በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት ከሚመዘግባቸው ድርጅቶች የአገልግሎት ክፍያዎችን ይሰበስባል፤ | 6) Collects service charges from organizations registered in accordance with regulations or directives issued pursuant to this Proclamation; |
| 7) አግባብነት ባላቸው ሕጎች ስለሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የድርጅቶችን መተዳደሪያ ደንቦችንና ማሻሻያዎቻቸውን ያረጋግጣል፤ ይመዘግባል፤ | 7) Certifies and records the bylaws of the organizations and their amendments, without prejudice to the provisions of the verification and registration of documents by the relevant laws; |
| 8) በክልሉ ብቻ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን ቁጥር፣ የተሰማሩባቸውን በታዎች፣ የሥራ ዘርፎች፣ የተጠቃሚዎቻቸውን እና የአባሎቻቸውን ብዛት እና መሰል መረጃዎች የሚይዝ የመረጃ ማዕከል ያቋቁማል፣ እንዲሁም እነዚህን መረጃዎች ይተነትናል፤ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ያሰራጫል፤ | 8) Establishes a data center that contains the number of registered organizations operating in the region, their thematic areas, project areas, the number of their beneficiaries and members, and similar information, and analyzes and distributes through various media. |
| 9) ድርጅቶች ሲፈርሱ በሒሳብ አጣሪነት የሚያገለግሉ ባለሙያዎችን ዝርዝር ከፋይናንስ ቢሮ ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፤ ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይቆጣጠራል፤ | 9) Prepares a list of experts who shall serve as accountants or auditors when organizations are dissolved, in cooperation with the finance Bureau |

10) የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎትን በተመለከተ ለሚመለከታቸው አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫና የማስረጽ ስራ ይሰራል፤

11) ለፍትሕ ቢሮ ከተሰጠዉ ሥልጣንና ተግባር እንደአስፈላጊነቱ ለዞን ፍትሕ መምሪያ ዉክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

12) በሕግ መሰረት ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

**11. የፋይናንስ ቢሮ ሥልጣንና ተግባራት**

የፋይናንስ ቢሮ በሌላ ህግ የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የመደራጀት መብትን በማይጻረር መልኩ ድርጅቶች ሊሠሩ የሚችሉባቸውን ከሥራ መስኮች አንጻር ቦታዎችን ይለያል፣ ምክረ ሀሳብ ይሰጣል ይደግፋል፤

2) የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚያቀርቡትን የኘሮጀክት ሰነድ የብቃት ግምገማ ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣ተቀባይነት ሲያገኝም ስምምነት ይፈራረማል፤

3) የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በገቡት የፕሮጀክት ስምምነት መሠረት ተግባራትን ስለማከናወናቸው በድጋፍና ክትትል ያረጋግጣል፣ በፕሮጀክት ዘመኑ ሁለት ጊዜ ወቅቱን የጠበቀ ግምገማ ያካሄዳል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፤

4) ከፍትሕ ቢሮ ጋር በቅንጅት ድርጅቶች በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ፣ ሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ እና የልማት እንቅስቃሴ

and monitors the proper performance of their duties;

10) Creates awareness to the concerned bodies promote regarding volunteerism;

11) May delegate such powers and duties to the Zonal Justice Department as necessary;

12) perform other duties necessary to carry out the purpose in accordance with law;

**11. Powers and function of Finance Bureau**

Without prejudice to the powers and functions given by other laws, the Bureau of Finance shall have the following powers and functions;

1) Identifies and makes recommendations in terms of areas where organizations can operate in a manner that does not contravene the right to association;

2) Conduct, execute, and sign an agreement upon approval of the project document submitted by civil society organizations;

3) Ensures support and monitoring of the implementation of activities in accordance with the project agreement entered into by civil society organizations; conducts periodic assessments and provides feedback twice during the project period;

ያላቸውን ሚና እንዲያጎለብቱ ያበረታታል፤ድጋፍ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

5) በፌዴራል ፍቃድ በክልሉ ፕሮጀክት ለመትግበር የሚንቀሳቀሱ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ፕሮጅክት ሰነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከሚመለክታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የፕሮጀክት ብቃተ ግምገማ ያካሂዳል፤ ስምምነት ይፈራርማል፤ ይከታትላል፤ ይገመግማል፤ አፈጻጸሙም በስታንዳርዱ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፤ ለሚመለክተዉ አካል ሪፖርተ ያቀርባል፤

6) በፌዴራል መንግስት ወይም በፍትሕ ቢሮ ተመዝግበው የመግባቢያ ሰነድ ወይም የፕሮጀክት ስምምነት ተፈራርመው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ተገቢውን አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆናቸው ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤ በህዝብ ጥቅምና መብት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ድርጊት እየፈጸሙ ከሆነ በፕሮጀክት ስምምነት መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣ የህግ ጥሰት ፈፅመው ሲገኙ ለመዘገበው አካል ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያሳውቃል፤

7) የመንግስትና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የጋራ የምክክር መድረክ ያዘጋጃል፤ያስፈጽማል፤

8) ዓመታዊ የኦዲትና የንብረት ቆጠራ ሪፖርት በክልሉ ፕሮጀክት ከሚተገበሩ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ይቀበላል፤ ግብረ መልስም ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

9) በዚህ አዋጅ የተቋቋመውን የሲቪል ማኅበረሰብ ፈንድ ያስተዳደራል፤

10) በፕሮጀክት ስምምነት መሠረት ለድርጅቶቹ ከቀረጥ ነጻ፣የመኖሪያ ፈቃድ እና የባንክ ሂሳብ እንዲከፈትላቸው እና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

11) ድርጅቶች የሚያከናዉኗቸዉ የልማት ሥራዎች ከመንግስት

4) In coordination with the Bureau of Justice, it encourages, supports, and monitors the role of organizations in democratic system building, human rights protection and development activities;

5) Conducts a project evaluation of the civil society organizations operating with Federal liscence to implement the project in the region together with the relevant stakeholders before the project document is put into operation; and signs agreement and follows, evaluates and ensures performance is up to standard and reports to the relevant body;

6) Provides support and monitoring for organizations that are registered with the federal government or the Justice Bureau and have signed a memorandum of understanding or project agreement and are providing appropriate services; If they are doing an act that harms the public interest and rights, they shall take the necessary measures according to the project agreement, and when they are found to have committed a violation of the law, they shall notify the party that registered it so that legal action should be taken;

7) Prepares and executes a joint consultation forum of government and civil society organizations;

8) Receives and provides feedback and supervises annual audit and inventory reports from civil society organizations implementing projects in the region;;

9)Adminsters the civil society fund established by this proclamation;

10) Provides tax-free, residence permit, bank

የልማት ዕቅድ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ድጋፍ ያደርጋል፤

12) የድርጅቶችን ፕሮጀክት በሚመለከት የሥራና የገንዘብ እንቅስቃሴ በውጭ ኦዲተሮች መመርመሩን ያረጋግጣል፤

13) በፌዴራልም ሆነ በክልሉ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን የፕሮጀክቶች ብዛት፣ ስርጭት፣ የተሰማሩበት ዘርፍ፣ የትግበራ ዘመን፣ የሀብት መጠን፣ የተፈጠረ የሥራ ዕድልና የተጠቃሚ ብዛት እና መሰል መረጃዎችን የሚያሳይ ዘመናዊ የመረጃ ቋት ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ያሰራጫል፤

14) ለፋይናንስ ቢሮ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ለዞን ፋይናንስ መምሪያ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

15) የአዋጁን ዓላማ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## ክፍል አራት

## የድርጅቶች አመሠራረትና ምዝገባ

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**12. መርሆዎች**

የድርጅቶች አመሠራረት በሚከተሉት መርሆች ይመራል:-

1) ማንኛውም ድርጅት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ሊቋቋም ይችላል፤

2) በድርጅቶች ውስጥ አባልነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው፤

3) አንድ አባል በፈለገ ጊዜ ከድርጅቱ መውጣት ይችላል፤

account opening and other support services to the organizations under the project agreement,

11) Supports the development activities carried out by the civil society organizations to be consistent with the development plan of the Government;

12) Ensures that work and financial activities related to the projects of civil society organizations are examined by external auditors;

13) It organizes, analyzes and distributes a modern database that shows the number of projects, distribution, sector in which they are engaged, period of implementation, amount of resources, created job opportunities and number of beneficiaries and similar information of the organizations registered and operating at the Federal aswelas Regional level;

14) May delegate such powers and duties to the Zonal Finance Department as necessary;

15) Performs other activities required to implement the purpose of this proclamation.

## SECTION FOUR

## ESTABLISHMENT and REGISTRATION of ORGANIZATIONS

### SUB SECTION ONE

### GENERAL PROVISIONS

**12. Principles**

The formation of organizations shall be governed by the following principles:

4) ማንኛውም ድርጅት አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሠረት በማድረግ የአባላት መቀበያ መሥፈርቶችን የመወሰን መብት አለው፤

5) ማንኛውም ሰው የድርጅቱን መስፈርት እስካሟላ ድረስ አባል የመሆን መብት አለው፤

6) እያንዳንዱ አባል እኩል ድምፅ አለው፤

7) ድርጅቶች ለአባላት ትርፍ ለማከፋፈል በማሰብ ሊቋቋሙ አይችሉም፤

8) የድርጅቶች አመሠራረትና የውስጥ አሰራር ዲሞክራሲያዊ መርሆዎችን የተከተለ፣ ከአድሎአዊነት የፀዳ፣ ነፃና ገለልተኛ ሊሆን ይገባል፤

9) ማንኛውም ድርጅት የሚመራው በመተዳደሪያ ደንቡ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ነው፤

10) ማንኛውም ድርጅት በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ካልሆነ በቀር አባላትን ሊቀበልና ሊያሰናብት አይችልም።

**13. ሀገር በቀል ድርጅቶች አመሰራረት**

ቁጥራቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች አገር በቀል ድርጅት ሊመሰርቱ ይችላሉ።

**14. የሀገር በቀል ድርጅት ዓይነቶች**

ለዚህ ክፍል ዓላማ የሀገር በቀል ድርጅት በሚከተለው አይነት አደረጃጀት ሊቋቋም ይችላል፡-

1) ማኅበር፣

2) ቦርድ-መር ድርጅት፣

1) Any organization may be established for a limited or indefinite period;

2) Membership in organizations shall be voluntary;

3) A member can leave the organization at any time;

4) Any organization has the right to determine the criteria for admission of members based on the relevant laws;

5) Anyone has the right to be a member as long as he meets the requirements of the organization;

6) Each member shall have an equal vote;

7) Organizations maynot be established with the intention of distributing profits to members;

8) The formation and internal governance of organizations shall be based on the democratic principles, non discriminatory, impartial and independent;

9) Any organization is managed by persons elected by the bodies authorized by the by memorandum of association;

10) Any organization cannot accept or dismiss members except in accordance with its memorandum of association.

**13. Establishment of local organizations**

Two or more people can form an Local Organization.

**14. Types of local organization**

3) የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት፣

4) የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት፣

5) የበጎ አድራጎት ኮሚቴ ናቸዉ።

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ማህበርና ቦርድ-መር ድርጅት

**15. ማኅበር**

1) ለዚህ ክፍል አላማ **"ማኅበር"** ማለት ቁጥራቸው አምስት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት የሚቋቋም እና ጠቅላላ ጉባዔው የበላይ ውሳኔ ሰጪ አካል የሆነበት ድርጅት ሲሆን ለዚህ ሕግ አፈጻጸም የሙያ ማህበራትን ይጨምራል፤

2) አንድ ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተርና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የሥራ ክፍሎች ያለው ሆኖ ሊደራጅ ይችላል፤ የማኅበሩ አወቃቀርና አስተዳደር በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

**16. ቦርድ-መር ድርጅት**

ለዚህ ክፍል አላማ ቦርድ-መር ድርጅት ቁጥራቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ መሥራቾች የሚቋቋም ሲሆን፡-

1) የድርጅቱ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አካል ቦርዱ ይሆናል፤

2) ቦርዱ ቁጥራቸው ከ5 እስከ 13 የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል፤

3) የመጀመሪያዎቹ የቦርዱ አባላት በመመሥረቻ ጽሑፉ ላይ በመሥራቾቹ ይሰየማሉ፤ የቦርድ አባላት የሥራ ዘመንና ከምሥረታ በኋላ የቦርድ አባላት የሚሰየሙበት ሥርዓት

For the purposes of this section, a local organization may be established under the following type of organization:

1) An association;

2) A Council-led Organization;

3) A charitable endowment;

4) A charitable trust; or

5) A Charitable Committee

## SUB SECTION TWO

## ASSOCIATIONS and COUNCIL LED ORGANIZATIONS

**15.Association**

1) For the purpose of this Sub-section An association is an organization formed by five or more members and governed by a General Assembly as the upper decision-making body; for the purpose of this Proclamation it shall include professional associations.

2) An association may have a General Assembly,Executive Committee, Manager, Auditor and other departments as may be necessary. Details regarding the structure and governance of an association shall be determined by its rules.

**16. Council-led Organization**

For the purpose of this sub-section Council-led organization means organization formed by two or more founders:

በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፤

4) ከድርጅቱ የሥራ መሪዎች ጋር የስጋ እና የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሰዎች የቦርድ አባል መሆን አይችሉም፤

5) ድርጅቱ ለቦርዱ ተጠሪ የሆነ ሥራ አስኪያጅ እና አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፣ ዝርዝሩ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅት

### 17. መሠረቱ

1) ለዚህ ክፍል አላማ **"የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት"** ማለት አንድ የተለየ ንብረት፣ ገንዘብ በስጦታ ወይም በኑዛዜ በዘላቂነትና በማይመለስ ሁኔታ ተለይቶ ለተገለጸ የበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ የሚውልበት ድርጅት ነው፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በስጦታ ወይም በኑዛዜ የሚሰጠው የንብረት ወይም የገንዘብ መጠን የበጎ አድራጎት አላማውን በመነሻነት ለማሳካት የሚያስችል መሆን አለበት፤

3) መሥራቹ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ተጠቃሚዎች ይወስናል፤ መሥራቹ ተጠቃሚዎቹን በበቂ ሁኔታ ካልወሰነ የሥራ አመራር ቦርዱ ከመሥራቹ ሀሳብ ጋር ይስማማል ብሎ በሚገምተው መልኩ ተጠቃሚዎችን ሊወስን ይችላል።

1) It's Board being the supreme decision making organ.

2) The Board shall have a minimum of five and a maximum of thirteen members.

3) The first Board members shall be designated by the founders. The term of service and appointment procedures for subsequent Council members shall be prescribed by the rules of the organization.

4) Persons who are related by consanguinity or affinity with officers of the organization may not be Board members.

5) A Council-led organization shall have a manager accountable to the Council and necessary staff as may be necessary. The particulars shall be determined by the bylaws of the organization.

## SUB SECTION THREE

## CHARITABLE ENDOWMENTS

### 17. The Basis

1) For the purpose of this Sub-section A "Charitable Endowment" is an organization by which a certain property is perpetually and irrevocably destined by donation, money or will for a purpose that is solely charitable.

2) Property or money provided through gift or will based on sub Article l of this provision shall be sufficient to fulfill the purpose the

| | |
|---|---|
| **18. ለምዝገባ ስለማመልከት**<br><br>1) መሥራቹ በሕይወት ሳለ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ምዝገባ የሚጠየቀው በመሥራቹ በራሱ ወይም ለዚህ ጉዳይ በወከለው ሰው ብቻ ነው፤<br><br>2) መሥራቹ ከሞተ በኋላ ጥያቄው የሚቀርበው ከመሥራቹ አደራ በተቀበለው ሰው ወይም የመሥራቹን ኑዛዜ በሚያስፈጽሙ ሰዎች ነው፤<br><br>3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱት በማይኖሩበት ጊዜ ለዘለቄታ ንብረትን ለበጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ውል ያዘጋጁ፣ ምስክር የሆኑ ወይም ውሉን በአደራ ያስቀመጡ ሰዎች የምዝገባ ጥያቄ ያቀርባሉ፤<br><br>4) በዚህ አንቀጽ መሠረት ምዝገባ የመጠየቅ ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች ምዝገባውን ሳይጠይቁ የቀሩ እንደሆነ መሥራቹ ከሞተ ከሦስት ወር በኋላ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ማንኛውም ይመለከተኛል በሚል ሰው አመልካችነት ወይም በፍትሕ ቢሮ አነሳሽነት ሊመዘገብ ይችላል፤<br><br>5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የሶስት ወራት ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ለበጎ አድራጎት ድርጅት ዓላማው የሚውለውን ገንዘብ ወይም ንብረት እና አጠቃላይ የምዝገባውን አካሔድ አስመልክቶ ዓላማውን የሚጻረር ተግባር ከተፈፀመ የፍትሕ ቢሮ በማንኛውም ጊዜ ጣልቃ መግባትና ማስተካከል ይችላል።<br><br>**19. ንብረትን ለዘለቄታ በጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት** | charity initially.<br><br>3) The founder shall determine the beneficiaries of a charitable endowment. Where the beneficiaries are not sufficiently determined by the founder, the Board may determine such beneficiaries as it deems consistent with the intentions of the founder.<br><br>**18. Application for Registration**<br><br>1) The registration of a Charitable Endowment may not be sought during the lifetime of the founder, except by the founder himself or a person delegated by the founder for that purpose.<br><br>2) After the death of the founder, it shall be sought by the person to whom the founder has entrusted such task and who has accepted it or by the executors of the founder's will .<br><br>3) In default of the persons specified in Sub-Article (1) and (2), it shall be sought by those persons who have drawn up the act of Endowment or who have been witnesses to it or who hold that act in deposit.<br><br>4) Where the persons who are bound to seek the registration of the Charitable Endowment fail to do so, the registration of the Charitable Endowment may be sought, three months after the death of its founder, by any interested party or by the Justice Bureau. |

**ተግባርን ስለመሻር**

ንብረትን ለዘለቄታ በጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ተግባር በፍትሕ ቢሮ ከመመዝገቡ በፊት መሥራቹ ሊሽረው ይችላል።

**20. የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅት አደረጃጀት**

ማናቸውም የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተርና ሌሎች አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች ይኖሩታል።

**21. የሥራ አመራር ቦርድ ጥንቅር**

1) የሥራ አመራር ቦርድ አባላት በመሥራቹ ወይም እርሱ በወከለው ሰው ይሾማሉ፤ የቦርድ አባላቱ በዚህ መልክ ካልተሾሙ የፍትሕ ቢሮ የሚሾሙበትን መንገድ ያመቻቻል፤

2) አንድ የሥራ አመራር ቦርድ አባል በማንኛውም ምክንያት ኃላፊነቱን መወጣት ካልቻለ በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አዲስ የቦርድ አባል ይሾማል፤

3) የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ቁጥር ከሦስት በታች ሊሆን አይችልም።

**22. የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣን እና ተግባራት**

1) የሥራ አመራር ቦርዱ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ የበላይ አካል ነው፤

2) የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን የሚመራ ሥራ አስኪያጅ

5) When any activity contrary to the aim of the registration or concerning the property or money and the whole registration process is occurred before the end of the three months indicated under sub Article 4 of this Article the Justice Bureau can intervene at any time.

**19. Revocation of an Act of Charitable Endowment**

The founder of an endowment may revoke it so long as the Charitable Endowment has not been registered by the Justice Bureau.

**20. Structure of Charitable Endowments**

Any Charitable Endowment shall be organized with the structure of Management Board, Manager, Auditor and other departments as may be necessary.

**21. Composition of the Management Board**

1) Members of the Management Board shall be appointed by the founder or by a person delegated by the founder. Where the founder or his delegated has not appointed members of the Management Board, the Justice Bureau shall facilitate the appointment of such members.

2) Where a member of management Boar is for any reason unable to perform his duties, a new member shall be appointed according to the rules of the Endowment.

3) The number of members of the Management

እና ኦዲተር ይሾማል፤ ያሰናብታል፤

3) የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ያስተዳድራል።

**23. የሥራ አመራር ቦርዱ ስብሰባዎች**

1) የሥራ አመራር ቦርዱ በዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በተመለከተው መሠረት ይሰበሰባል፤

2) የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ውሳኔዎችን የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል።

**24. ለሥራ አመራር ቦርድ አባላት የሚፈፀሙ ክፍያዎች**

1) በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ካልተወሰነ በስተቀር አንድ የቦርድ አባል በአባልነቱ ክፍያ አያገኝም፤

2) በቦርድ ስብሰባ ላይ ለመገኘት አንድ አባል ያወጣውን ወጪ ለመሸፈን የሚደረግ ማካካሻ እንደ ክፍያ አይቆጠርም።

**25. የሥራ አስኪያጁ ሥልጣን እና ተግባራት**

የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ፡-

1) የዘለቄታ በጎ አድራጎት የድርጅቱን ሥራ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ይመራል፤

2) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ድርጅቱን ይወክላል፤

3) የሥራ አመራር ቦርዱ ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

4) የሥራ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የሥራ እና የሒሳብ ሪፖርቶችን ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፤

5) የድርጅቱን ገቢ የሚያሳድጉ ሁኔታዎችን ያጠናል፣ በሥራ አመራር

Board shall in no case be less than three.

**22. Powers and Functions of the Management Board**

1) The Management Board shall be the supreme organ of the Chairtable Endowment and shall have the following powers and functions:

2) Appoint a Manager who shall be responsible to manage the Endowment or dismiss the same; and

3) Administer the Endowment in accordance with its rules.

**23. Meetings of the Management Board**

1) The Management Board shall meet as prescribed by the rules of the Charitable Endowment.

2) The decisions of the Management Board shall be taken by majority.

**24. Remuneration of Management Board Members**

1) A member of the Management Board shall not be entitled to remuneration unless a provision about his entitlement to remuneration has been made, by the Charitable Endowment's rules.

2) Payments made in connection with covering costs incurred by Management Board Members for the purpose of attending Council meeting shall not be considered as remuneration.

**25. Powers and Functions of the Manager**

The manager of the Charitable Endowment shall :

ቦርዱ ሲፀድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤

6) በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት በድርጅቱ ሥም የተከፈቱ የባንክ ሂሳቦችን ያንቀሳቅሳል፤

7) ሌሎች በሥራ አመራር ቦርዱ የሚሰጡትን ተያያዥ ተግባራት ያከናውናል።

**26. የኦዲተር ሥልጣን እና ተግባራት**

የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ኦዲተሩ፡-

1) የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል፤

2) የድርጅቱን የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ የሒሳብ አያያዝ መርሆዎች መሠረት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል።

**ንዑስ ክፍል አራት**

**የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት**

**27. መሠረቱ**

ለዚህ ክፍል ዓላማ **"የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት"** ማለት የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን በሚያቋቁመው ሠነድ መሠረት አንድ የተለየ ንብረት ለበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ እንዲውል በባለአደራዎች የሚተዳደር ድርጅት ነው።

**28. አመሠራረት**

1) የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት በስጦታ፣ በኑዛዜ ወይም

1) Direct the work of the Charitable Endowment pursuant to its bylaws;

2) Represent the Endowment in all its dealings with the third parties;

3) Follow up and supervise the implementation of the decisions of the Management Board;

4) Submit work plan and budget as well as activity and financial reports to the Management Board;

5) Study conditions that shall promote income generation for the Endowment and implement such where approved by the Management Board;

6) Operate bank accounts opened in the name of the Endowment in accordance with its bylaws; and

7) Discharge other related tasks which may be given to him by the Management Board.

**26.Powers and Functions of the Auditor**

The Auditor of Charitable Endowment shall :

1) Monitor the financial and proprietary administration of the Charitable Endowment;

2) Prepare the internal audit report of the organization in accordance with accounting standards acceptable in Ethiopia;

**SUB SECTION FOUR**

**CHARITABLE TRUST**

**27. The Basis**

አግባብ ባለው የመንግስት አካል ውሳኔ ሊቋቋም ይችላል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ስጦታ ወይም ኑዛዜ አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይመራል፤

3) የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ማቋቋሚያ ሰነድ መሥራቹን፣ ባለአደራዎቹንና የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ተጠቃሚዎች በግልጽ ለይቶ ማስቀመጥ አለበት።

**29. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ቀጣይነት**

1) የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ሊቋቋም ይችላል፤

2) ላልተወሰነ ጊዜ የተቋቋመ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ዘላቂና ቋሚ ይሆናል።

**30. በባለአደራዎች የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ**

1) የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት መሥራች የሆነ ሰው ባለአደራዎቹን መሾም አለበት፤

2) ባለአደራዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52 በተደነገገው መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ለፍትሕ ቢሮ የምዝገባ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

3) የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት የምዝገባ ጥያቄ ድርጅቱ በተመሠረተ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል፤

4) ባለአደራዎቹ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከማግኘታቸው በፊት በስጦታው ወይም በኑዛዜው ላይ የተመለከተውን

For the purpose of this Sub-section □Charitable Trust□ is an organization established by an instrument by which specific property is constituted solely for a charitable purpose to be administered by persons, the trustees, in accordance with the instructions given by the instrument constituting the charitable trust.

**28. Formation**

1) A Charitable Trust may be established by a donation or by a will or by the decision of the concerned government body.

2) A donation or shall under Sub-Article (1) of this Article shall be governed by the relevant provisions of civil code.

3) A document which established a charitable trust shall clearly specify the founder, the trustees and beneficiaries of the charitable trust.

**29. Perpetuity of a Charitable Trust**

1) A Charitable Trust may be established for a definite or an indefinite period.

2) Where a Charitable Trust is established for an indefinite period, it shall be perpetual and irrevocable.

**30. Application for Registration by Trustees**

1) The founder of a charitable trust shall appoint trustees.

2) The Trustees shall apply to the Agency for

ሀብት ባለይዞታነት ወይም ባለቤትነት ወደ አደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለማስተላለፍ ከሚያስፈልጉ ድርጊቶች በስተቀር በሀብቱ ላይ ሦስተኛ ወገኖችን የሚያካትት ማናቸውንም ድርጊት መፈፀም አይችሉም።

**31. የባለአደራዎች ብዛት**

1) የባለአደራዎች ብዛት ከሦስት ያነሰ እና ከአምስት የበለጠ ሊሆን አይችልም። ከሦስት ያነሱ ሰዎች ተሹመው ከሆነ ይህን መመዘኛ ለማሟላት ፍትሕ ቢሮ ቀሪዎቹ ባለአደራዎች የሚሾሙበትን መንገድ ያመቻቻል፤

2) ከአምስት በላይ ባለአደራዎች ተሾመው ከሆነ በቅድሚያ የተጠቀሱት መሥራት የሚችሉና ፈቃደኝነት ያላቸው አምስት ሰዎች ብቻ ባለአደራ ይሆናሉ፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም አንድ ወይም ከዚያ በላይ ድርጅቶች በባለአደራነት ተሾመው ከሆነ የባለአደራዎቹ ብዛት ከሦስት በታች እንዲሆን ፍትሕ ቢሮ ሊፈቅድ ይችላል፤

4) በዚህ አንቀጽ መሠረት ከሚሾሙት ባለአደራዎች ቢያንስ አንዱ መደበኛ መኖሪያው በክልሉ ውስጥ መሆን አለበት።

**32. የባለአደራዎች አሿሿም**

1) ባለአደራ የሚሾመው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ያቋቋመው ሰው ወይም እርሱ የወከለው ሰው ነው፤ እነዚህ ሰዎች ከሌሉ ፍትሕ ቢሮ ባለአደራ የሚሾምበትን መንገድ ያመቻቻል፤

2) የተሾመው ባለአደራ ይህን ኃላፊነት አልቀበልም ካለ ወይም በማናቸውም ምክንያት ባለአደራነቱን ማከናወን ካልቻለ

a certificate of registration in the manner provided in Article 52 of this Proclamation.

3) An application for the registration of a Charitable Trust shall be submitted within 3 months from the formation of the Charitable Trust.

4) The trustees may not perform any acts involving third parties before acquiring a certificate of registration except those acts necessary for transferring the resource mentioned in the donation or shall to the possession or ownership of the Charitable Trust.

**31. Number of Trustees**

1) The number of trustees shall not in any case be lower than three and more than five. Where less than three persons are appointed, the Justice Bureau shall facilitate the appointment of the number of people required to fulfill this requirement.

2) Where more than five persons are appointed, as Trustees, the five first named persons who are able and willing to act shall alone be the trustees.

3) Notwithstanding sub-Article (1) of this Article, the Justice Bureau may allow less than 3 persons as trustees where one or more of such trustee is a Charity.

በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ሌላ ባለአደራ ይሾማል።

**33. ድርጅትን በባለአደራነት መሾም**

1) መሥራቹ ሕጋዊ ሰውነት ያለውን ድርጅት በባለአደራነት ከሾመ የተሾመው ድርጅት ሥራ መሪዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ያስተዳድራሉ፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ድርጅት የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን በኑዛዜው፣ በስጦታው ወይም በፍትሕ ቢሮ ትዕዛዝ በተወሰነው መሠረት ከሌሎች ስጦታዎች ወይም ዓላማውን ለማሳካት ከሚጠቀምበት ገቢ ለይቶ በመያዝ ያስተዳድራል።

**34. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደረጃጀት**

1) የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ፣ ገንዘብ ያዥ እና ኦዲተር በመሥራቹ ወይም መሥራቹ በወከለው ሰው ይሾማሉ፤

2) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን ኃላፊዎች መሥራቹ ወይም በመሥራቹ የተወከለው ሰው ያልሾመ እንደሆነ ባለአደራዎቹ ከመካከላቸው ወይም ከውጭ ኃላፊዎቹን ይሰይማሉ፤

3) ባለአደራዎቹ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ኃላፊዎቹን ያልሰየሙ እንደሆነ ኃላፊዎቹ በፍትሕ ቢሮ ይሾማሉ፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም፣ ባለአደራዎች ኃላፊነታቸውን በጋራ ያከናውናሉ፤

5) ባለአደራዎቹ ስብሰባቸውን የሚመራ ሊቀመንበር

4) At least one of the Trustees appointed under this Article shall be from domiciliary of the Region.

**32. Appointment of Trustees**

1) The Trustees may be appointed by the person who founded the Trust or by the person designated by him. In the absence of such appointment the Justice Bureau shall facilitate the appointment of Trustees.

2) Where the Trustee so appointed refuses his agency or is for any other reason unable to perform the trusteeship, a new trustee shall be appointed according the bylaws of the trust.

**33. Appointment of an organization as a Trustee**

1) If the founder has appointed an organization which has a legal personality as a Trustee, the officers of the appointed organization shall administer the trust.

2) The organization provided in Sub-Article (1) of this Article shall administer the charitable trust by the terms of the will, donation or order of the Justice Bureau and shall distinguish it from other donations or income that it utilizes to achieve its purposes.

**34. Structure of a Charitable Trust**

1) The manager, treasurer and auditor of a charitable trust shall be appointed by the founder or a person delegated by the

ከመካከላቸው ይመርጣሉ።

**35. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አስተዳደር**

1) ከባለአደራዎች በጽሑፍ ተቃውሞ እስካልቀረበ ድረስ ሥራ አስኪያጁ የሌሎች ባለአደራዎች ስምምነት ሳያስፈልገው የማስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፤

2) ከማስተዳደር ሥራዎች ውጭ ያሉና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተቃውሞ የቀረበባቸው ውሣኔዎች ከባለአደራዎች ውስጥ ቢያንስ ሦስቱ በተገኙበት ስብሰባ በድምፅ ብልጫ ይወሰናል፤

3) ከባለአደራዎች ውስጥ እኩል ድጋፍ ያላቸው የተለያዩ ሃሣቦች ሲቀርቡ የመጨረሻው ውሣኔ ሰብሳቢው በሚሰጠው ድምፅ ይወሰናል፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሠረት በተሰጡ ውሳኔዎች የማይስማሙ ባለአደራዎች የልዩነት ሃሣባቸው በቃለ ጉባኤው ላይ እንዲመዘገብላቸው መጠየቅ ይችላሉ።

**36. የባለአደራዎቹ ኃላፊነት**

1) ባለአደራዎች ከአንድ መልካም የቤተሰብ አስተዳዳሪ በሚጠበቀው ትጋትና ጥንቃቄ ድርጅቱን ማስተዳደር አለባቸው፤

2) የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በተቋቋመበት ሠነድ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ባለአደራዎቹ ከፋይናንስ ቢሮ ፈቃድ ውጭ የድርጅቱን ንብረት ለሌላ ሰው ሊያስተላልፉ አይችሉም፤

founder.

2) If these officers are not appointed by the founder, delegated by his delegatee, the trustees shall designate the same from among themselves or third parties.

3) If the trustees have not appointed the officers in accordance with sub-article 2 of this article, the officers shall be appointed by the Bureau of Justice;

4) Notwithstanding the provisions of sub-Article 1 of this Article, trustees shall discharge their duties jointly;

5) The Trustees shall elect a chairman from among themselves to preside over their meetings.

**35. Administration of a Charitable Trust**

1) Unless the trustees object in writing, the manager shall perform management functions without the consent of the other trustees;

2) Decisions that are outside the scope of management and to which objections have been made in accordance with Sub-Article 1 of this Article shall be decided by a majority vote at a meeting attended by at least three of the trustees;

3) When different ideas with have equal support are presented among the trustees, the final decision shall be determined by the vote of the chairperson of the meeting;

4) Trustees who disagree with decisions made pursuant to sub-Articles 2 and 3 of this Article

3) ባለአደራዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ንብረት ያለ ዋጋ ለሌላ ሊያስተላልፉ አይችሉም፤

4) ባለአደራዎቹ በአደራ በጎ አድራጎት ሥራ መሪነታቸው ከሥልጣናቸው በላይ በፈጸሙት ተግባር ወይም በሰጡት ውሳኔ በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ፤ ሆኖም በአንቀጽ 35 ንዑስ ቁጥር 4 መሠረት ከውሳኔው መለየቱን ያስመዘገበ ባለአደራ በውሳኔው ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም።

**37. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅትን ስለመወከል**

1) ሥራ አስኪያጁ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ይወክላል፤

2) ሥራ አስኪያጁ በእርሱ ምትክ ድርጅቱን የሚወክለውን ባለአደራ ይመርጣል፤ ማናቸውም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ጉዳዮች የሚከታተል ጠበቃ ሊወክል ይችላል፤

3) ባለአደራዎቹ ከሥልጣን ወሰናቸው ሳያልፉ ለፈፀሟቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ተጠያቂ የሚሆነው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ነው።

**38. የማቋቋሚያ ሰነዱ ትዕዛዞች**

1) የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ካቋቋመው ሰነድ የተቀበላቸውን ግልጽ የሆኑ ትዕዛዞች ባለአደራው መከተል አለበት፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ተጠቃሚ ለሆነው ሰው ጥቅም የሚያስፈልግ ሆኖ የታየ እንደሆነ ከተባሉት ትዕዛዞች ውጪ ለመሥራት ባለአደራው ከፍትሕ ቢሮ ፈቃድ መጠየቅ ይችላል።

may request that their dissenting opinion be recorded in the minutes of the meeting.

**36. Responsibilities of the Trustees**

1) Trustees shall administer the Trust with due diligence and care expected from a good paterfamilias.

2) The Trustees may not transfer the assets of the organization to another person without the permission of the Bureau of Finance, unless the Charitable Trust issues a press release at the time of its establishment.

3) The Trustees may not alienate the property of a Charitable Trust by a gratuitous title.

4) The Trustees shall be jointly and severally liable for any damage caused to the Charitable Trust by any act or decision they make in the course of their charitable work, beyond their authority; however, a Trustee who has registered his dissent opinion from the decision the trustees in accordance with Article 35, Sub-paragraph 4, shall not be liable for any damage caused by the decision.

**37. Representation of a Charitable Trust**

1) The Trustee manager shall represent the Charitable Trust;

2) The Trustee manager shall delegate the trustee and may also appoint an advocate to represent the Charitable Trust in any proceedings;

3) The Charitable Trust shall be liable for

**39. ለባለአደራዎች የሚፈፀም ክፍያ**

1) የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በተቋቋመበት ሠነድ ወይም በማናቸውም ሌላ ሕግ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር አንድ ባለአደራ ክፍያ የማግኘት መብት አይኖረውም፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም አንድ ባለአደራ ለአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለሰጠው ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን በመወከል ለፈጸመው ሙያዊ አገልግሎት ክፍያ ሊፈጸም እንደሚገባ ሁሉም ባለአደራዎች በጽሁፍ ሲስማሙ እና ፍትሕ ቢሮ ሲያፀድቅ ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሀብት ተመጣጣኝ ክፍያ ያገኛል፤

3) የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ አንድ ባለአደራ በግሉ ያወጣቸው ወጪዎች እንዲተኩለት የመጠየቅ መብት አለው።

**40. የባለአደራው ሥራ መልቀቅ**

1) ባለአደራው ሥራ የመልቀቅ ሀሳብ ካለው ሥራውን ከመልቀቁ ከሁለት ወር በፊት ለሌሎች ባለአደራዎች ሊያሳውቅ ይገባል፤ ይህን ሳያስታውቅ ቢቀር ከዚህ የተነሣ በአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ላይ ለሚደርሰው ኪሣራ ኃላፊ ይሆናል፤

2) ባለአደራው ሥልጣኑን ለሌላ ባለአደራ እስከሚያስተላልፍ ድረስ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት፤

3) አንድ ባለአደራ የሥራ መልቀቂያ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የማስጠንቀቂያ

acts of trustees within the scope of their authority.

**38. Order of Establishment Document**

1) A trustee shall adhere to the orders under the establishment document of the trust.

2) Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1 of this Article, the Trustee may request permission from the Bureau of Justice to operate beyond the orders on the establishment document when it is essential to do so for the interest of its beneficiaries.

**39. Remuneration of Trustees**

1) A trustee shall not be entitled to receive any remuneration unless expressly provided for in the establishment document or by law;

2) Notwithstanding Sub-Article 1 of this Article, a trustee shall be entitled to receive reasonable remuneration out of the trust funds for any services that he provides on behalf of the Trust, if all the trustees agree in writing and the Justice Bureau approves;

3) A trustee has the right to claim reimbursement for personal expenses incurred in connection with the management of the Charitable Trust.

ጊዜ ከማለፉ አንድ ወር አስቀድሞ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ባቋቋመው ሰው ወይም ይህን ለመፈጸም ሥልጣን በተሰጠው ሰው ወይም እነዚህ ባይኖሩ በፍትሕ ቢሮ አዲስ ባለአደራ ይሾማል።

**41. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ንብረት ማስያዝ**

1) የተጠቃሚዎች ባለገንዘቦች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ንብረት ወይም ተጠቃሚው ሊያገኝ የሚገባውን አበል በማናቸውም ሁኔታ ማስያዝ አይችሉም፤

2) ለተወሰነ ጊዜ የተቋቋመ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ሲፈርስ ንብረቱን የመውሰድ መብት ያላቸው ባለገንዘቦች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ንብረት ማስያዝ ይችላሉ።

**42. የተጠቃሚዎች መብት**

1) ተጠቃሚዎች በአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ማቋቋሚያ ሠነድ መሠረት የሚገባቸው ጥቅም እንዲሰጣቸው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ሊጠይቁ ይችላሉ፤

2) ተጠቃሚዎች መብቶቻቸውን የሚጎዳ ሁኔታ ሲፈጠር ባለአደራው እንዲሻር ወይም ተገቢ የሆነ ዋስትና እንዲሰጥ ፍትሕ ቢሮን መጠየቅ ይችላሉ፤

3) ተጠቃሚዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ አካል በሆኑ ንብረቶች ላይ በግልም ሆነ በጋራ የማዘዝ ወይም የማስተዳደር መብት የላቸውም፤

**4)** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ቢኖርም እነዚህን ንብረቶች በሚመለከት የይርጋ ዘመን እንዲቋረጥ

**40. Resignation of a Trustee**

1) If the trustee intends to resign, he must notify the other trustees two months before resigning; if he fails to do so, he will be liable for any losses incurred by the Charitable Trust under his trust;

2) A trustee shall remain responsible for the administration of the charitable trust until he hands over the trusteeship;

3) If a Trustee submits a resignation request, a new Trustee shall be appointed by the person who established the Charitable Trust or by the person authorized to do so, or, in their absence, by the Bureau of Justice, one month before the expiration of the notice period stipulated in Sub-Article 1 of this Article.

**41. Attaching Charitable Trusts**

1) The creditors of beneficiaries may in no case attach a Charitable Trust or any allowance to which a beneficiary is entitled.

**2)** When a charitable trust established for a specific period of time is dissolved, the creaditors of the property who have the right to take possession of the property may seize or attach the property of the charitable trust.

**42. Rights of Beneficiaries**

1) The beneficiaries may request the

ማድረግን በመሳሰለው ሥራ መብቶቻቸውን የመጠበቅ ሥራዎችን ብቻ መፈፀም ይችላሉ።

**ንዑስ ክፍል አምስት**

**ስለበጎ አድራጎት ኮሚቴ**

**43. መሠረቱ**

ለዚህ ክፍል አላማ **"የበጎ አድራጎት ኮሚቴ"** ማለት ቁጥራቸው አምስት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት ለበጎ አድራጎት ዓላማ ከሕዝብ ለመሰብሰብ ሀሳብ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው።

**44. የበጎ አድራጎት ኮሚቴን ስለማፅደቅ**

1) የበጎ አድራጎት ኮሚቴ በፍትሕ ቢሮ ሳይፀድቅ ገንዘብም ሆነ ንብረት ማሰባሰብ ወይም ማናቸውም ድርጊት መፈፀም አይችልም፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ኮሚቴውን ለማቋቋም በሚደረጉ አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

3) የፍትሕ ቢሮ የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎችን ሲያፀድቅ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 50 እና 53 ድንጋጌዎች በማገናዘብ መወሰን አለበት።

**45. የሒሳብ መግለጫ**

1) የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ዓመታዊ የሒሳብ መግለጫ ለፋይናንስ ቢሮ ማቅረብ አለበት፤

Charitable Trust to provide them with the benefits they are entitled to in accordance with the Charitable Trust's establishment document;

2) Beneficiaries may request the Justice Bureau to revoke the trustee or provide appropriate guarantees when a situation arises that violates their rights;

3) Beneficiaries do not have the right to individually or jointly control or manage the assets that are part of the Charitable trust;

4) Notwithstanding the provisions of Sub-Article 3 of this Article, beneficiaries of a Charitable Trust may only perform acts to protect their rights, such as suspending the period of limitations on such Assets.

**SUB SECTION FIVE**

**CHARITABLE COMMITTEES**

**43. The Basis**

For the purposes of this section, a **"charitable committee"** means a group of five or more persons who have the intention of collecting money or other property from the public for charitable purposes.

**44. Approval of Charitable Committees**

1) A charity committee may not raise funds or

2) የበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተቋቋመው ከአንድ ዓመት ላነሰ ጊዜ ከሆነ ይህ ጊዜ እንዳለቀ የሒሳብ መግለጫ ማቅረብ አለበት።

**46. የበጎ አድራጎት ኮሚቴ አደረጃጀት**

1) የበጎ አድራጎት ኮሚቴን የሚያቋቁም ውሳኔ መሥራች አባላቱን፣ የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ፕሬዚዳንት፣ ገንዘብ ያዥና ኦዲተር ዝርዝር ሁኔታ ማሳየት ይኖርበታል፤

2) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ውሳኔው የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ሥራዎች እንዴት መከናወን እንዳለባቸው መወሰን እና በኮሚቴው የሚሰበሰበውን ገንዘብ እና ንብረት መጠንና አጠቃቀሙን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ማስቀመጥ ይኖርበታል። ዝርዝሩ ፋይናንስ ቢሮ ከፍትሕ ቢሮ ጋር በመሆን በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

**47. የአባላት ኃላፊነት**

1) ከበጎ አድራጎት ኮሚቴው እንቅስቃሴ ለሚመነጩ ግዴታዎችና ዕዳዎች አባላት በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ፤

2) የአባላት ግዴታዎችንና ዕዳዎች በተመለከተ የፍትሕ ቢሮ፣ የዘርፍ አስተዳዳሪው፣ ማናቸውም ለጋሽ፣ አባል ወይም ተጠቃሚ በኮሚቴው አባላት ላይ ክስ የማቅረብ መብት አላቸው።

**48. በቂ ያልሆነ ገንዘብና ንብረት**

1) በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብና ንብረት የኮሚቴውን ዓላማ ለማሳካት በቂ ካልሆነ ወይም ዓላማውን ማሳካት የማይቻል ከሆነ ይህ ገንዘብ ወይም ንብረት የኮሚቴው መቋቋም በፀደቀበት ውሳኔ ላይ

property or carry out any other activity without the approval of the Justice Bureau;

2) Sub-article (1) of this Article shall not apply to the activities necessary to establish the Charitable Committee;

3) When approving Charitable Committees, the Bureau of Justice shall take into consideration the provisions of Articles 50 and 53 of this Proclamation;

**45. Statement of Accounts**

1) A Charitable committee shall submit its annual statement of accounts to the Finance Bureau;

2) A Charitable committee shall submit its statement of accounts at its dissolution where the period for which the charitable committee is formed is less than one year.

**46. Structure of a Charitable committee**

1) The resolution establishing a Charitable Committee must list the founding members, the President, Treasurer, and Auditor of the Charity Committee;

2) Where necessary, the resolution shall determine how the activities of the Charitable Committee shall be carried out and shall establish necessary measures to control the amount and use of funds and property collected by the Committee. The details shall be determined by the directives to be issued by the Finance Bureau in collaboration with the Justice Bureau.

በተመለከተው መሠረት በሥራ ላይ ይውላል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በፀደቀው ውሳኔ ውስጥ የተመለከተ ነገር ከሌለ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ለስጦታ አድራጊዎቹ ተመላሽ ይሆናል፤

3) ለበጎ አድራጎት ኮሚቴው ገንዘብ ወይም ንብረት የሰጡ ሰዎች መልሰው ሊወስዱት ካልፈለጉ ወይም ካልቻሉ ወይም የማይታወቁ ከሆኑ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት በፋይናንስ ቢሮ እና ፍትሕ ቢሮ ውሳኔ ለተመሳሳይ የበጎ አድራጎት ዓላማ ይውላል።

**49. ቀሪ ገንዘብና ንብረት**

1) በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት ዓላማውን ለማሳካት አስፈላጊ ከሆነው በላይ ከሆነ ቀሪው ገንዘብ ወይም ንብረት ኮሚቴው ባፀደቀው ውሳኔ መሠረት ለሌላ ተመሳሳይ የበጎ አድራጎት ዓላማ ሥራ ላይ ይውላል፤

2) በውሳኔው ውስጥ ይህንን በሚመለከት የተገለፀ ነገር የሌለ እንደሆነ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ፋይናንስ ቢሮ እና ፍትሕ ቢሮ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለሌላ ለተመሳሳይ የበጎ አድራጎት ዓላማ እንዲውል ይወስናሉ።

**50. ወደ ዘላቂ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ስለመለወጥ**

1) የበጎ አድራጎት ኮሚቴው በፀደቀበት ውሳኔ ላይ በተመለከተው መሠረት በኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት ለአንድ ለተወሰነ ዘላቂ ዓላማ የሚውል ከሆነ ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት ዘላቂ የበጎ አድራጎት ድርጅት

**47. Liability of Members**

1) The members of a Charitable Committee shall be jointly and severally liable for obligations and debts arising from the activities of Charitable Committee;

2) The Justice Bureau, the Sector Administrator, any donor, member, or beneficiary have the right to file a lawsuit against the committee members regarding the obligations and debts of the members.

**48. Insufficient Fund and Property**

1) If the funds and assets collected by the Charitable Committee are insufficient to achieve the objectives of the Committee or if it is impossible to achieve the objectives, such funds or assets shall be used in accordance with the decision approving the establishment of the Committee;

2) Unless otherwise provided in the decision adopted under Sub-Article 1 of this Article, the money or property shall be returned to the donors;

3) If the persons who donated money or property to the Charity Committee do not want to take it back or are unable to do so, or if they are unknown, it shall be used for the same charitable purpose at the discision of the Finance Bureau and the Justice Bureau in accordance with the provisions of this Proclamation.

**49. Balance**

1) Where the funds or assets collected by the Charitable Committee exceed those necessary to achieve its purpose, the remaining funds or assets shall be used for another similar charitable purpose in accordance with a

ይቋቋማል፤

2) በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት የታቀደውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ ከሆነው መጠን በላይ ከሆነ የኮሚቴው አባላት በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅትነት ለመመዝገብ ሊያመለክቱ ይችላሉ፤

3) ኮሚቴው በድርጅትነት ከተመዘገበ፣ በኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብና ንብረት ወደተመዘገበው ዘላቂ በጎ አድራጎት ድርጅት ይተላለፋል።

**ንዑስ ክፍል ስድስት**

**ኅብረቶችና የኅብረቶች ኅብረት**

**51. ኅብረቶችና የኅብረቶች ኅብረት አመሠራረት**

1) ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ወይም ኅብረቶች የጋራ ዓላማቸውን ለማሳካት በመካከላቸው በሚያደርጉት ስምምነት ወይም በዚህ ሕግ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ኅብረት ወይም የኅብረቶች ኅብረት መመስረት ይችላሉ፤

2) ኅብረቶች ወይም የኅብረቶች ኅብረት ከአባሎቻቸው መብትና ጥቅም ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ሕጋዊ ዓላማ ለማሳካት ሊመሠረቱ ይችላሉ፤ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል:-

ሀ/ ለጋራ ግቦች ስኬታማነት አባሎቻቸውን ማስተባበርና መደገፍ፤

ለ/ የሀሳብ፣ የመረጃ እና የልምድ ልውውጥን ማካሄድ፤

ሐ/ የአባላትን አቅም መገንባትና ሀብት የማሰባሰብ

decision approved by the Committee;

2) If there is no specific provision in the decision, the Finance Bureau and the Justice Bureau shall determine that the money or property is used for another similar charitable purpose in accordance with the provisions of this Proclamation.

**50. Change into a Charitable Endowment**

1) Where under the decision approving the Charitable committee the money or property collected by the Charitable committee is to be destined to a specific lasting object, a Charitable Endowment shall be constituted for the attainment of such object.

2) Where the money or property collected by the charitable committee is significantly larger than what is necessary for the attainment of the proposed purpose, the members of a Charitable committee may seek permission and apply to the Justice Bureau for registration as civil society organization.

3) If the Committee is registered as an organization, the money or property collected by the Committee shall be transferred to the Charitable Endoment.

**SUB SECTION SIX**

**CONSORTIA AND CONSORTIUM OF CONSORTIUMS**

51. **Formation of a Consortium and a Consortium of Consortiums**

ጥረታቸውን መደገፍ፤

መ/ የአባላትን ሥነ ምግባርና የሙያ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎችን ማከናወን፤

ሠ/ የአባላት የጋራ ድምፅ በመሆን የአባላትን የጋራ መብትና ጥቅም ማስከበር እና ለአባላት ምቹ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር መሟገት፤

ረ/ አባሎቻቸው በተሠማሩበት የሥራ ዘርፍ የጥናትና ምርምር፣ የፖሊሲ ሙግት እና ድጋፍ ሥራዎችን ማከናወን።

3) ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱት ዓላማዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ኅብረት አባል ድርጅቱ ከሚሰራበት የሥራ ዘርፍ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሥራ በመሥራት ከአባሉ ጋር ውድድር ውስጥ ሊገባ አይችልም፤ ሆኖም ኅብረቶች ሀብት በማሰባሰብ በአባሎቻቸው አማካኝነት የፕሮጀክት ሥራዎችን ማከናወን ይችላሉ።

## ንዑስ ክፍል ሰባት

## የድርጅቶች ምዝገባ

### 52. ምዝገባ

1) ማንኛውም ድርጅት በዚህ ሕግ መሠረት በፍትሕ ቢሮ መመዝገብ አለበት፤

2) ፍትሕ ቢሮ ለቀረበው የምዝገባ ማመልከቻ በቀረበለት በ15 ቀናት ውስጥ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ አመልካች ድርጅቱን በመመዝገብ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

1) Two or more civil society organizations or consortiums may form a consortium or a consortium of consortiums in accordance with an agreement concluded among themselves towards the achievement of their objectives or in accordance with the provisions of this Proclamation.

2) Consortiums or a consortium of consortiums may be established for any legal purpose related to rights and benefits of their members including those indicated below:

   a/ To support their members for the achievement of common objectives;

   b/ To facilitate the sharing of ideas, information and experience;

   c/ To build the capacity of members and support their resource mobilization efforts;

   d/ To undertake activities designed to enhance the ethical and professional standards among members;

   e/ To work for the protection of the rights of members by articulating their common voice and advocate for enabling work environment for members;

   f/ To conduct research and policy advocacy activities in the sectors in which their members operate.

3) Notwithstanding the above mentioned aims, a consortium may not involve itself in operations that place it in direct competition with a member organization. However, consortiums are not barred

3) አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያልተሰጠው እንደሆነ በ15 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለፍትሕ ቢሮ ሃላፊ ማቅረብ ይችላል፤

4) የፍትሕ ቢሮ ሃላፊ የቀረበለትን ቅሬታ በመመርመር በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤

5) ፍትሕ ቢሮ ሃላፊ ድርጅቱ ያልተመዘገበው ያለበቂ ምክንያት መሆኑን ሲረዳ የምዝገባ ሰርተፊኬቱ ወዲያውኑ እንዲሰጥ ያዛል። ለዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም ፍትሕ ቢሮ ለቀረበለት የምዝገባ ማመልከቻ በንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው ጊዜ ምላሽ ካልሰጠ ድርጅቱን ላለመመዝገብ በቂ ምክንያት እንደሌለው ይቆጠራል፤

6) በፍትሕ ቢሮ ሃላፊ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔው በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ለጉባዔው ይግባኝ ማለት ይችላል፤

7) በጉባዔው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል።

**53. ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሰነዶች**

1) የሀገር በቀል ድርጅቶች የምዝገባ ማመልከቻ በድርጅቱ መሥራቾች ሰብሳቢ ተፈርሞ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች ማካተት ይኖርበታል፡-

from collecting and mobilizing resources to operate projects through their member organizations.

**SUB SECTION SEVEN**

**REGISTRATION of ORGANIZATIONS**

**52. Registration**

1) Any organizations shall be registered by the Bureau of Justice in accordance with these provisions;

2) The Bureau of Justice shall, upon application and after ensuring the fulfillment of the requirements stipulated under this Proclamation, register the applicant and issue a registration certificate within 15 days from the date of application;

3) Where the Justice Bureau fails to issue certificate of registration within the period indicated under sub-Article 2 of this Article, the applicant may file its complaint to the Head of Justice Bureau within 15 days from the expiry of such period;

4) The Head of Justice Bureau shall examine the complaint and make a determination on the matter within a period of 30 days;

5) Where the Head of Justice Bureau finds that the directorate failed to register the organization without a good cause, it shall direct the directorate to issue the certificate of registration forthwith. For the purpose of this provision, the Justice Bureau shall be deemed not to have a good cause to refuse registration if it

ሀ/ የመሥራቾችን ሥም፣ አድራሻና ዜግነት የያዘ የምሥረታ ቃለ-ጉባኤ፣

ለ/ የመሥራቾች የታደሰ የመታወቂያ ወይም ጊዜዉ ያላለፈበት የፓስፖርት ኮፒ፣

ሐ/ የድርጅቱን ሥም እንዲሁም ዓርማ (ካለው)፣

መ/ የድርጅቱን ዓላማ እና ሊሰማራ ያሰበበትን የሥራ ዘርፍ፣

ሠ/ ሊሰማራ ያሰበበትን የሥራ ቦታ፣

ረ/ በመሥራቾች የፀደቀ መተዳደሪያ ደንብ፣

ሰ/ የድርጅቱን አድራሻ፤

2) የኅብረቶች የምዝገባ ማመልከቻ በተወካያቸው ድርጅት ኃላፊ አማካኝነት ተፈርሞ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ ይቀርባል፡-

ሀ/ በኅብረቱ መሥራች ድርጅቶች ተወካዮች የተፈረመ የመተዳደሪያ ደንብ፣

ለ/ አባላት ኅብረቱን ለመመሥረት የተስማሙበት ቃለ-ጉባዔ፣

ሐ/ ለኅብረቱ አባላት ከክልሉ ፍትሕ ቢሮ ወይም ከስር መዋቅር የተሰጠ የአባላት የምዝገባ የምስክር ወረቀት፤

3) አመልካቹ አግባብነት ባለው ደንብ የሚወሰነውን የምዝገባ ክፍያ ይከፍላል፤

fails to respond to such application within the time limit mentioned under sub Article 2 of this Article.

6) An applicant who is dissatisfied with the decision of the Head of the Justice Bureau may appeal to the Council within 15 days of receiving the decision;

7) An applicant who is dissatisfied with the decision of the council may appeal to the High Court within 30 days of receiving the decision.

**53. Documents Required for Registration**

1) An application for registration by local organizations shall be signed by the Chairperson of the founders of the organization and contain the following particulars:

a/The minutes of the formative meeting indicating the names, addresses and citizenship of the founders;

b/Copy of the identity card or passport of the founders;

c/The name of the organization and its logo, if it has one;

d/ The objectives of the organization and its intended sector of operation;

e/ The region where it intends to operate;

f/ The rules of the organization approved by the founders;

g/ The organization’s address;

2) Applications for registration of a consortium

4) የሙያ ማኅበራት ምዝገባ እና አስተዳደር ዝርዝር ጉዳዮችን በተመለከተ ጉባዔው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**54. የምዝገባ ጥያቄን አለመቀበል**

1) ፍትሕ ቢሮ ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ መኖሩን ካረጋገጠ ድርጅቱን አይመዘግብም፡-

ሀ/ ማመልከቻው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተደነገጉትን መስፈርቶች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝና ይህንንም እንዲያስተካክል የአመልካቹ ተወካይ ተጠይቆ ለማስተካከል ካልቻለ፣

ለ/ የድርጅቱ ዓላማ ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተመለከተው የሥራ ዝርዝር ለሕግ ወይም ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ ከሆነ፣

ሐ/ ድርጅቱ የሚመዘገብበት ሥም ወይም ዓርማ ከሌላ ድርጅት ወይም ከማንኛውም ሌላ ተቋም ሥም ጋር የሚመሳሰል ከሆነ ወይም ሕግን ወይም የሕዝብን ሞራል የሚቃረን ከሆነ፣

መ/ ድርጅቱ ለምዝገባ ያቀረበው ሰነድ በሐሰት የተዘጋጀ ወይም የተጭበረበረ ከሆነ፤

2) በዚህ ሕግ በግልጽ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጪ ፍትሕ ቢሮ በአሰራርም ይሁን መመሪያ በማውጣት የምዝገባ ጥያቄን ሊከለክል አይችልም፤

3) ፍትሕ ቢሮ ማመልከቻውን በዚህ ሕግ መሠረት መርምሮ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ አመልካቹ የጎደለውን ነገር በ15 ቀናት ውስጥ አስተካክሎ እንዲያቀርብ በጽሑፍ መልስ ይሰጠዋል፤

4) አመልካቹ የተባለውን ነገር ለማስተካከል ፈቃደኛ ካልሆነ ፍትሕ ቢሮ ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ሕጋዊ

shall be signed by the head of their representative organization and submitted together with the following documents:

a/ Rules of the consortium signed by the representatives of founder organization;

b/ The minutes of the decision among members to form the consortium;

c/ A certificate of registration issued by the Justica Bureau or authorized zonal government body to the members of the consortium.

3)The applicant shall pay the registration fee as determined by the relevant regulations;

4) The Civil Society Organizations Council may issue directives on details regarding the registration and administration of professional associations

**54. Refusal of Application for Registration**

1) The Agency shall refuse to register an organization where it finds that:

a/ The application does not comply with the necessary conditions set out under Article 10 of this Proclamation and the applicant's representative fails to meet such conditions after being requested to do so;

b/ The aim of the organization or the activities described under the organization's rules are contrary to law or public moral;

c/ The name or symbol under which the proposed organization is to be

ምክንያት በመጥቀስ ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል፤

5) የምዝገባ ጥያቄው ውድቅ የሆነበት አመልካች በውሳኔው ቅር ከተሰኘ ቅሬታውን በ15 ቀናት ውስጥ ለፍትሕ ቢሮ ሃላፊ ማቅረብ ይችላል፤

6) የፍትሕ ቢሮ ሃላፊ ቅሬታው በቀረበለት በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

7) አንድ ድርጅት በማታለል ወይም በማጭበርበር የምዝገባ የምስክር ወረቀት አግኝቶ ከሆነ ይኸው በፍትሕ ቢሮ ሲረጋገጥ የፍትሕ ቢሮ ሃላፊ ድርጅቱ እንዲፈርስ ሊወስን ይችላል፤

8) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5 እና 6 መሠረት በተሰጠ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ድርጅት ውሳኔው በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ይግባኙን በመሥራቾቹ አማካኝነት ለጉባኤው ማቅረብ ይችላል፤

9) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት በተሰጠ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ድርጅት የጉባኤው ውሳኔ በደረሰው 30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን በመሥራቾቹ አማካኝነት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

**55. የመተዳደሪያ ደንብ አስፈላጊነትና ይዘት**

1) ማንኛውም ድርጅት የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የመተዳደሪያ ደንብ ሊኖረው ይገባል፡-

ሀ/ የድርጅቱ ስም፣

ለ/ የድርጅቱ ዓላማዎች፣

ሐ/ የድርጅቱ የበላይ አካል፣ ሥልጣንና ተግባር፣ የውስጥ

registered resembles the name of another organization or any other institution or is contrary to public moral or is illegal;

d/ The document furnished for registration by the organization is fraudulently obtained or forged.

2) The Justice Bureau may not refuse applications for reasons other than those specified under this on the basis of practice or directive.

3) If the Justice Bureau examines the application in accordance with this law and finds it inadmissible, it shall provide the applicant with a written response requiring him to correct the deficiencies within 15 days;

4) If the applicant unwilling to correct the matter, the Justice Bureau shall reject the request, citing the legal reason for not accepting the application;

5) An applicant dissatisfied with the Justice Bureau's decision may lodge a complaint before the Head of Justice Bureau within 15 days from receiving the decision.

6) The Head of Justice Bureau shall review the compliant and give a decision with in 30 days up on reciving the compliant.

7) If an organization obtained a registration certificate by fraudulent or forgery act and if it is verified by the Justice Bureau, the Head of Justice Bureau shall decide dissolussion of the Organization.

8) If the organization is unsatisfied with the Head of Justice Bureau's decision that is given in accordance with sub Article 5 and 6 of this Article, the organization may lodge an appeal before the Council within 15 days from receiving the decision.

9) If the organization is unsatisfied with the

አደረጃጀትና አስተዳደር፣ የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት፣

መ/ የድርጅቱ ገቢና ሐብት ለአባላት እንዲሁም ለሠራተኞች በሕግ ከተፈቀደ የአገልግሎት ክፍያ በቀር ሊከፋፈል የማይችል መሆኑን፣

ሠ/ የድርጅቱ አባል ወይም ሠራተኛ በመሆኑ ብቻ በድርጅቱ ንብረት ላይ አንዳችም መብት የማይኖረው መሆኑን፣

ረ/ ድርጅቱ ከአባላት የተለየ የራሱ መለያና የሕግ ሰውነት ያለው መሆኑን፣

ሰ/ የአባላት መለዋወጥ በድርጅቱ ሕልውና ላይ ተጽዕኖ የሌለው መሆኑን፣

ሸ/ አባልነት በውርስ የማይተላለፍ መሆኑን፣

ቀ/ የድርጅቱ የሒሳብና የገንዘብ እንቅስቃሴ ተቀባይነት ባለው የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት የሚመራ መሆኑን፣

በ/ የድርጅቱን የሥራና የሒሳብ ዕቅድና አፈጻጸም የሚመረምረውና የሚያጸድቀው የበላይ አካል መሆኑን፣

ተ/ መተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻልበትን ሥርዓት፣

ቸ/ የድርጅቱን የበጀት ዓመት፣

ኀ/ ድርጅቱ እንዲፈርስ ወይም እንዲዘጋ የሚወስነውን የበላይ

Council’s decision that is given in accordance with sub Article 8 of this Article, the organization may lodge an appeal before the Regional High Court within 30 days from receiving the Council’s decision.

**55. Importance and contents of bylaws**

1) All organizations must have rules containing the following:

a/ The organization’s name

b/ The organization’s objectives

c/ The organization’s executive body, power and functions, internal governance and structure, meeting and decision-making procedures

d/ A stipulation indicating that the organization’s income and resources may not be distributed to members or employees except for payment of legally permitted service fees;

e/ A stipulation indicating that the organization’s members or employees do not have an automatic right over the organizations resource only by the mere fact of their membership ;

f/ A stipulation indicating that the organization has a separate and independent legal personality and symbol from its members;

g/ A stipulation indicating that Change of Members of the organization do not have effect on the existence of the organization;

h/ Membership does not devolve by inheritance;

አካልና የሚመራበትን ሥርዓት፣

ነ/ ድርጅቱ ሲፈርስ ያለበትን ሕጋዊ ዕዳ ከፍሎ ቀሪው ገንዘብና ንብረት የድርጅቱ የበላይ አካል ለመረጠው ሌላ ድርጅት ወይም በክልሉ ፍትሕ ቢሮና በክልሉ ፋይናንስ ቢሮ በኩል ለሌላ አካል ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት ለተቋቋመው ፈንድ የሚተላለፍ መሆኑን፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የመተዳደሪያ ደንቡ የሚከተሉትንም ሊያካትት ይችላል፤

ሀ/ ለአባልነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣

ለ/ አባልነት የሚቋረጥባቸውን ወይም የሚታገድባቸውን ምክንያቶች፣

ሐ/ አባልነት ሲቋረጥ ወይም ሲታገድ በድርጅቱ ውስጥ ይግባኝ የሚጠየቅበት ሥርዓት፣

መ/ የአባልነትና ሌሎች ክፍያዎች የሚወሰኑበትና የሚጠየቁበት ሥርዓት፣

ሠ/ የሥራ አመራር ኃላፊዎች የሚሾሙበትና የሚሻሩበት ሥርዓት፣ ሥልጣንና ተግባራት፣

ረ/ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት የሚሾምበትና የተጠሪነት ሥርዓት፣ ሥልጣንና ተግባራት፣

ሰ/ በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ የሚሰማራ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ፣

3) የፍትሕ ቢሮ ድርጅቶች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ሞዴል

i/ The organization's accounts and financial transactions shall be managed by an accepted accounting system;

j/ The supreme body of the organization shall examine and approve the organization's financial and work plan and performance;

k/ Procedure for amending the rules;

l/ The organization's budget year;

m/ The body that decides on the dissolution of the organization, and the procedures to be followed;

n/ A stipulation indicating that during dissolution, once the debts of the organization are paid the remaining money and property shall be transferred to another organization named by the organization's higher body or to another body by the decision of Justice and Finance Bureau or to the fund established under this proclamation.

2) In addition to the information mentioned above under sub Article 1, the bylaws of the organization may also include:

a/ Requirements that must be fulfilled for membership

b/ Reasons for termination or suspension of membership

c/ Internal procedures for appealing from decisions to terminate or suspend membership;

መተዳደሪያ ደንቦችን ሊያዘጋጅ ይችላል።

**56. የምዝገባ ውጤት**

በዚህ ሕግ የተመለከቱትን መስፈርት አሟልቶ የተመዘገበ ድርጅት፡-

1) የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፤

2) በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ ውል ይዋዋላል፤

3) ልዩ የሥራ ፈቃድን የሚመለከቱ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በማናቸውም ሕጋዊ የሥራ መስክ የመሰማራት መብት አለው፤

4) በሰሙ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት የመሆን፣ ንብረት የማስተዳደርና የማስተላለፍ መብት አለው፤ ሆኖም ንብረቱም ሆነ ከንብረቱ ሽያጭ የሚገኘው ገንዘብ በስጦታ ለአባላት ጥቅም ወይም ከአላማው ውጪ ለሆነ ተግባር ሊተላለፍ አይችልም፤

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት ንብረት ያስተላለፈ ድርጅት በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለፍትሕ ቢሮ እና ለፋይናንስ ቢሮ ማሳወቅ አለበት።

**57. የሥራ ነፃነት**

1) በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ድርጅት የተቋቋመበትን ሕጋዊ ዓላማ ለማሳካት በክልሉ በየትኛውም ሕጋዊ ሥራ ላይ የመሠማራት ሙሉ መብት አለው፤

2) ማንኛውም ድርጅት በራሱ የፕሮጀክት ሥራ ለማከናወን

d/ Procedures for imposing and collecting membership and other fees;

e/ The power, procedure for appointment and removal of executive members of the organization;

f/ The powers and functions and procedure for the appointment and accountability of the officers of the organization;

g/ Whether or not the organization performs fundraising activities ;

3) The Justice Bureau may prepare model rules of Organization.

**56. Result of Registration**

Any organization which registered upon fulfillment of the registration requirements provided in this Proclamation:

1) Shall have legal personality;

2) Can sue, be sued and enter into contracts;

3) Without prejudice to laws that require special license, can operate in the sector of its choice;

4) To own, administer and transfer movable and immovable property. However, the proceeds from the disposal of the property may not be transferred as donation for the benefit of members or to another activity which is not its mission:

5) The organization which transfer property based on sub Article 4 of this Article shall

ወይም ለሌሎች ድርጅቶች ወይም ህዝባዊ ተቋማት የገንዘብ፣ የዓይነትና የዕውቀት ድጋፍ ለማድረግ ሊቋቋም ይችላል፤

3) በባለስልጣኑ የተመዘገቡ ድርጅቶች በተቻለ መጠን በክልሉ ከሚሠሩ አገር በቀል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ተቋማት ጋር በአጋርነት በመሥራት የአቅም ማጎልበቻ ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ፤

4) በክልሉ ውስጥ የሚሠሩ ድርጅቶች በራሳቸው የፕሮጀክት ሥራዎች ለማከናወን ወይም ከሌሎች መንግሥታዊ ካልሆኑ ሀገር በቀል ድርጅቶች ጋር የገንዘብ፣ የዓይነትና የዕውቀት ድጋፍ በማድረግ መሥራት ይችላል፤

5) ድርጅቶች በክልሉ ውስጥ ከሚያከናውኗቸው ሥራዎች ጋር ግንኙነት ወይም ተያያዥነት ያላቸውን፣ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ አሰራሮች እንዲለወጡ፣ እንዲሻሻሉ ወይም አዲስ ሕጎችና ፖሊሲዎች እንዲወጡ ሐሳብ ማቅረብ ይችላሉ፤

6) ለጠቅላላው ሕዝብ ወይም ለሦስተኛ ወገን ጥቅም ማንኛውም ድርጅት የሚያከናውናቸው ሥራዎች ዘላቂ ልማትን የሚያመጡና ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት የሚያስችሉ ወይም የአባላቶቹን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ ወይም የተሰማሩበትን የሙያ መስክ ለማሳደግ አስተዋጽዖ ያለው እንዲሆን ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፤

7) ማንኛውም የሙያ ማህበር የአባላቶቹን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ ወይም የተሰማሩበትን የሙያ መስክ ለማሳደግ አስተዋጽዖ ያለው እንዲሆን ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፤

inform to the Justice Bureau and Finance Bureau within 15 days.

**57. Operational Freedom**

1) An organization shall have the right to engage in any lawful activity to accomplish its objectives.

2) An organization may be established to implement project activities on its own or to provide financial, inkind and technical support to other organizations.

3) Organizations registered by the authority can support capacity building by working in partnership with local organizations and governmental institutions working in the region as much as possible;

4) Organizations working in the region can carry out their own projects or work with other non-governmental local organizations with financial, in-kind and knowledge support;

5) The Organization may propose recommendations for the change or amendment of existing laws, policies or practices, or issuance of new laws and policies in the region which have relationship with the activities they are performing;

6) For the benefit of the general public or a third party, any organization shall make the necessary efforts to ensure that its activities help to bring about sustainable

8) ለጠቅላላው ሕዝብ ወይም ለሦስተኛ ወገን ጥቅም መሥራትን ዓላማ አድርጎ የተቋቋመ ድርጅት፣ የሴቶችን፣ ህጻናትን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአረጋውያንንና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ ወይም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጥቅምን ማካተቱን ማረጋገጥ አለበት፤

9) ማንኛውም ድርጅት ከተመዘገበ በኋላ በሌላ ሕግ የተለየ ፈቃድ እንደሚያስፈልጋቸው በተመለከቱ የሥራ ዓይነቶች ከሚመለከታቸው የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ተገቢውን ፈቃድ ሳያገኝ ወደሥራ መግባት አይችልም፤

10) የማንኛውም ድርጅት አባል፣ አመራርና ሠራተኞች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የድርጅቱን ጥቅም የማስቀደምና ከእነሱ ጥቅም ጋርም እንዳይጋጭ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

**58. የሀብት አሰባሰብ እና አስተዳደር**

1) ማናቸውም ድርጅት፡-

ሀ/ ለሚተገብረው ፕሮጀክት ዘላቂነት አስፈላጊ በመሆናቸው፣ ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ፕሮጀክቱ ከሚፈጸምበት ቦታ እንዳይወጡ በፕሮጀክት ስምምነቱ ላይ በግልጽ ከተመለከቱ ንብረቶች በስተቀር፣ ንብረቱን በክልሉ ውስጥ የማንቀሳቀስ ሙሉ መብት አለው፤

ለ/ ለዓላማው መሳካት ገቢ ለማግኘት በማንኛውም ሕጋዊ የንግድና ኢንቨስትመንት ሥራ ውስጥ አግባብነት ባላቸው የንግድና ኢንቨስትመንት ሕጎች መሠረት የመሳተፍ መብት አለው። ሆኖም ከሥራው የሚገኘውን ትርፍ ለአባላት

development, contribute to the democratization process, promote the rights and interests of its members or enhance the profession they are engaged in;

7) Any professional association must make appropriate efforts to protect the rights and interests of its members or to contribute to the development of the professional field in which they are engaged;

8) An organization which is established for the benefit of the general public or third parties shall ensure that its activities take into account the interests of women, Children, persons with disabilities, the elderly and others exposed to threat or vulnerable groups of the society.

9) Any organization cannot engage in sectors which require additional permit by law without getting the necessary permit from the relevant government bodies.

10) In performing their duties all members, officers and employees of the organization have the responsibility to give primacy to the organization's interest and take the necessary precaution to avoid conflict of interest.

**58. Resource Mobilization and Administration**

1) Any Organization:

a/ Shall have the right to move its properties with in the Region, unless

ጥቅም ማስተላለፍ አይችልም፤

ሐ/ ለዓላማው መሳካት ከየትኛውም ሕጋዊ ምንጭ ገንዘብ የመጠየቅ፣ የመቀበልና የመጠቀም መብት አለው።

2) ለጠቅላላው ሕዝብ ወይም ለሦስተኛ ወገን ጥቅም መሥራትን ዓላማ አድርጎ የተቋቋመ ድርጅት የአስተዳደር ወጪው ከገቢው ከ20 በመቶ ሊበልጥ አይችልም፤

3) ለንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ አፈጻጸም "የአስተዳደር ወጪ" ማለት ድርጅቱ ከሚያከናውነው የፕሮጀክት ሥራ ጋር ተያያዥነት የሌለው ነገር ግን ለድርጅቱ ሕልውና ቀጣይነት አስፈላጊ የሆነ እና ከአስተዳደር ሥራዎች ጋር የተያያዘ ወጪ ሆኖ፡-

ሀ/ የአስተዳደር ሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅሞችን ፣

ለ/ ከአስተዳደር ሥራ ጋር የተያያዘ የአላቂና ቋሚ እቃዎች ግዢን፣

ሐ/ የጥገናና እድሳት ወጪዎችን፣

መ/ የቢሮ ኪራይ፣

ሠ/ የፓርኪንግ ክፍያዎች፣

ረ/ የኦዲት አገልግሎት፣

ሰ/ የማስታወቂያ ክፍያ፣

ሸ/ የባንክ አገልግሎት፣

ቀ/ የመብራት፣ የስልክ፣ የፋክስ፣ የውሃ፣ የኢንተርኔት፣ የፖስታና የሕትመት አገልግሎት ወጪዎችን፣

በ/ የግብር፣

ተ/ ለአስተዳደር ሥራ የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ግዢ፤ ጥገና፤ የነዳጅና ዘይት እንዲሁም የመድኅን ግዢ ወጪዎችን፣

the Project Agreement states that such properties may not be transferred because they are necessary for the sustainability of a specific project it is implementing.

b/ Have the right to engage in any lawful business and investment activity in accordance with the relevant trade and investment laws in order to raise funds for the fulfillment its objectives. However, the profit to be obtained from such activities may not be transferred for the benefit of members.

c/ Shall have the right to solicit, receive and utilize funds from any legal source to attain its objective.

2) The Administrative cost of an organization established for the benefit of the general public or that of third Parties may not exceed 20 percent of its total income.

3) For the purpose of sub Article 2, "Administrative Expense" shall mean expenses which are not related to the project activities of an organization but are necessary to ensure the continuity of an organization and related to administrative activities, and shall include:

a/ salaries; and benefits of administrative employees;

b/ Purchase of capital and fixed assets related to administrative work,

c/ repair and maintenance expenses ;

d/ office rent,

የቅጣት ክፍያዎችን፤

ቸ/ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን ያካትታል፤

4) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 የተደነገገው በልዩ ሁኔታ ተፈጻሚ የማይሆንባቸውን ድርጅቶች በሚመለከት የፍትሕ ቢሮ ከፋይናንስ ቢሮ ጋር በመተባበር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**59. በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ስለመሠማራት**

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሠረት በገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ የሚሰማራ ድርጅት፣ አግባብነት ባላቸው የንግድ ፈቃድና ምዝገባ ህጎች መሠረት አዲስ የንግድ ድርጅቶችን ወይም ኩባንያዎችን በማቋቋም፣ በነባር የንግድ ድርጅቶች ውስጥ አክሲዮን በመያዝ፣ ህዝባዊ መዋጮ በመሰብሰብ ወይም የንግድ ስራን በብቸኛ ባለቤትነት በማካሔድ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን ማከናወን ይችላል፤

2) ድርጅቱ በራሱ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን በሚያከናውንበት ጊዜ ለዚሁ ስራ የተለየ የባንክ ሒሳብ መክፈት እንዲሁም በንግድ እና ታክስ ህጉ በሚጠየቀው መሠረት የገቢ ማስገኛ ስራውን የሚመለከት የተለየ የሂሳብ መዝገብ መያዝ ይኖርበታል፤

3) አግባብነት ያላቸው የታክስ፣ የንግድ ፈቃድና ምዝገባ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ሕጎች በገቢ ማስገኛ ስራዎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

4) ድርጅቱ ከገቢ ማስገኛ ስራው የሚያገኘው ገቢ የድርጅቱን የአስተዳደር እና የፕሮግራም ወጪዎች ለመሸፈን ይውላል፤

5) ድርጅቱ ከገቢ ማስገኛ ስራው የሚያገኘው ገቢና ሃብት

e/ parking fees,

f/ audit fees,

g/ advertisement expenses,

h/ bank service fees,

i/ fees for electricity, fax, water and internet services; postal and printing expenses;

j/ tax,

k/ purchase and repair of vehicles for administrative purposes, and procurement of oil and lubricants for the same; insurance costs, Penalty payments

l/ attorney fees.

4) The JusticeBureau in cooperation with Finance Bureau may issue directives regarding organizations exempted from the application of provisions of sub Article 2 and 3 of this Article.

**59. Income Generation Activities**

1) An organization which engages in income generating activities in accordance with Article 58(1)(b) of this Proclamation may do so by establishing a separate business organization (company), acquiring shares in an existing company, collect public collections or operating its business as a sole proprietorship.

2) An organization engaged in income generating activities shall open a separate bank account and keep separate books of

| | |
|---|---|
| ለአባላት እንዲሁም ለሠራተኞች ሊከፋፈል አይችልም፤<br><br>6) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ድርጅቶች ህዝባዊ መዋጮ ሲሰበስቡ ለፍትሕ ቢሮ እና ለፋይናንስ ቢሮ ማሳወቅ አለባቸው፤<br><br>7) በዚህ አንቀፅ መሰረት በገቢ ማስገኛ ስራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ለፍትሕ ቢሮ እና ለ ፋይናንስ ቢሮ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ማሳወቅ አለባቸዉ።<br><br>**60. በሽያጭ ስለማስተላለፍ**<br><br>ማንኛውም ድርጅት ወይም ማኅበር ንብረቱን ለማናቸውም ሶስተኛ ወገን በሽያጭ ሲያስተላልፍ ለህዝብ ጥቅም ሲባል ከቀረጥ ነጻ የገባ ንብረት ከሆነ ሽያጩ በሀገሪቱ የጉምሩክ ህግ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።<br><br>**61. በሥራ መሪነት ወይም በቦርድ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት መሥራት የማይችሉ ሰዎች**<br><br>1) ማንኛውም ሰው በአንድ ድርጅት ውስጥ በሥራ መሪነት ወይም በድርጅቱ የቦርድ ወይም ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት መሥራት የማይችለው:-<br><br>ሀ/ በማታለል ወይም ታማኝነትን በማጓደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣና ያልተሰየመ ከሆነ፣<br><br>ለ/ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የሲቪል መብቱን የተገፈፈና መብቶቹ ያልተመለሱለት ከሆነ፣ | account for its business in accordance with the relevant commercial and tax laws.<br><br>3) The relevant tax, commercial registration and business licensing, and investment laws shall be applicable to income generation activities under this provision.<br><br>4) Income that is generated from income generating activities shall be used to cover administrative and program costs of the organization.<br><br>5) The income and resources that are acquired from income generating activities shall not be transferred or shared for the benefit of members or workers of the organization.<br><br>6) When the organizations collect public collections based on sub Article 1 of this Article, they shall inform to the Justice Bureau and Finance Bureau.<br><br>7) An organizations engaged in income generating activities based on this Article shall inform to the Justice Bureau and Finance Bureau within fifteen days.<br><br>**60. Transfer by sale**<br><br>When any company or organization sells its property to any third party, if it is tax-free property for public benefit, the sale shall be enforced according to the customs law of the country. |

ሐ/ በሕግ መሠረት ከችሎታ ማጣት የተነሳ መሥራት የማይችል ከሆነ፣

መ/ በፍርድ ቤት ክልከላ የተደረገበት ከሆነ ነው፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የማናቸውም ድርጅት የቦርድ ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆነ ሰው በዚያው ድርጅት ውስጥ የሥራ መሪ ወይም ተቀጣሪ ሠራተኛ ሆኖ መሥራት አይችልም፤

3) የድርጅቱ የምዝገባ ማመልከቻ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በመጣስ የቀረበ ከሆነ የክልሉ ፍትሕ ቢሮ ድርጅቱን አይመዘግብም።

**62. የድርጅቶች መዝገብ**

1) ፍትሕ ቢሮ ድርጅቶች የሚመዘገቡበት መዝገብ ይይዛል፤

2) በፍትሕ ቢሮ ትክክለኛ ቅጂ ስለመሆኑ የተረጋገጠ የመዝገቡ ሙሉ ወይም ከፊል ግልባጭ በማናቸውም የክርክር ሂደቶች በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል፤

3) ፍትሕ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡትን እንዲሁም የታገዱትንና ከመዝገብ የተሠረዙትን ድርጅቶች ዝርዝር በየዓመቱ በጋዜጣ ያወጣል።

**63. የድርጅት ቅርንጫፍ**

1) ማንኛውም ድርጅት አስቀድሞ ለፍትሕ ቢሮ በማሳወቅ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለሚከፈት ቅርንጫፍ የሚሰጠው ሥልጣን ራሱን የቻለ ድርጅት የሚያደርገው ወይም

**61.Persons Who shall not Serve as Officer or Members of Board's Management Committee**

1) No person shall act as an Officer or Council Management Committee Member of an Organization or a branch thereof if that person:

a/ has been convicted of a crime that involves fraud or dishonest crime acts and has not been reinstated;

b/ has been convicted of any crime and deprived of his civil rights and not yet been restored;

c/ unable to act by reason of legal interdiction;

d/ Has been judicialy interdicted.

2) Without prejudice to the provisions of Sub-Article 1 of this Article, a person who is a member of the board or executive committee of any organization may not work as a manager or employee in that same organization;.

3) If the application for registaration submitted by the Organization is contrary to the rules under sub Article 1 and 2 of this Article, the Agency shall not register the Organization.

**62. Register of Organizations**

1) The Justice Bureau shall keep a register of organizations.

2) A full or partial copy of the record, certified

ዋናው መስሪያ ቤት በቂ ቁጥጥር እንዳያደርግበት የሚከለክል ሊሆን አይችልም።

**64. ለውጥን ስለማሳወቅ**

1) ማንኛውም ድርጅት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ለውጥ ሲያደርግ ለፋይናንስ ቢሮና ፍትሕ ቢሮ ማሳወቅና ማስመዝገብ አለበት፡-

ሀ/ የስያሜ ወይም የምልክት ለውጥ፣
ለ/ የሥራ ዘርፍ ለውጥ፣
ሐ/ የዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ ለውጥ፣
መ/ የሥራ ቦታ ለውጥ፣
ሠ/ የሥራ አመራር አባላትና የሥራ መሪ ለውጥ፣
ረ/ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የሚደረግ ማናቸውም ለውጥ፤
ሰ/ የባንክ ሒሳብ ወይም ፈራሚዎች ለውጥ፤

2) በዚህ አንቀጽ መሠረት የተደረገ ለውጥ የድርጅቱን ማናቸውም መብቶች ወይም ግዴታዎች አይነካም።

**65. የምስክር ወረቀትን በይፋ ስለማሳየት**

1) ማንኛውም ድርጅት የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን በዋናው መስሪያ ቤት እንዲሁም ግልባጩን በየቅርንጫፎቹ ለማናቸውም ጎብኚ ሊታይ በሚችል ቦታ ማስቀመጥ ይኖርበታል፤

2) የድርጅቱ ስምና መለያ ምልክት በድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤትና ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ለሕዝብ ሊታይ በሚችል ግልጽ ስፍራ መቀመጥ ይኖርበታል።

**66. ሕልውናን ስለማረጋገጥ**

1) ማንኛውም በፍትሕ ቢሮ የተመዘገበ ድርጅት በዚህ አዋጅ

as a true copy by the Bureau of Justice, shall be admissible as evidence in any litigation proceedings;

3) The Justice Bureau shall publish every year, in an official Gazzette, the list of Organization registered, suspended or cancelled under this Proclamation.

**63. Branch of an Organization**

1) An organization may establish a branch based on its rules by giving prior notice to the Justice Bureau.

2) The powers of the branch of the organization established under Sub-Article (1) of this Article shall not make it an independent organization on its own or prevent the head office from making sufficient control on the branch.

**64.Obligation to inform Changes**

1) If an organization makes changes to any of the following matters, it shall inform the Finance Bureau and Justice Bureau about the change or amendment and get it registered.

a/ Change of its name or symbol,

b/ Change of organization's operational sector,

c/ Change of Head quarters,

d/ Change the location of operation,

e/ Change of executive members or chief executive,

f/ Amendments of its rules,

g/ Change of bank account or signatories.

2) A change under this Article shall not affect any rights or obligations of the Organizations.

ውስጥ ሪፖርት ለማቅረብ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ባለፈ በሦስት ወራት ውስጥ ሪፖርት ካላቀረበ ፍትሕ ቢሮ የድርጅቱን ሕልውና ለማረጋገጥ በጋዜጣ ጥሪ ያደርጋል፤

2) ከላይ የተመለከተው ጥሪ በጋዜጣ በወጣ በ30 ቀናት ውስጥ ድርጅቱ በርግጥም ሕልውና ያለው ከሆነ የድርጅቱ ሕጋዊ ተወካይ ቀርቦ በዚህ ሕግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ፍትሕ ቢሮ ሪፖርት ያላቀረበበትን ምክንያት ማስረዳት ይጠበቅበታል፤

3) ተወካዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ድርጅቱ ሪፖርት ያላደረገበትን በቂ ምክንያት ካላቀረበ የፍትሕ ቢሮ ኃላፊ ጉዳዩን ለጉባኤው አቅርቦ ድርጅቱ እንዲፈርስ ያስወስናል፤

4) ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ከፕሮጀክት ትግበራ ጋር በተያያዘ ማንኛዉም ድርጅት በዚህ አዋጅ ዉስጥ ሪፖርት ለማቅረብ የተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ለፋይናንስ ቢሮ ማቅረብ አለበት።

## ክፍል አምስት

## ሒሳብና ሪፖርት

### 67. የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ

1) ማናቸውም ድርጅት የድርጅቱን የገንዘብ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ተቀባይነት ባለው የሒሳብ አሰራር የተዘጋጀ የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት፤

2) የሒሳብ ሰነዶቹ የድርጅቱን ገቢና ያወጣውን ወጪ፣ የወጪውን ምክንያት፣ ሐብትና ዕዳ፣ የለጋሾችን ማንነትና

### 65. Publicly Displaying a Certificate

1) Every organization shall keep its certificate of registration in its Head Office and a copy thereof in its branches in a place that is visible to any visitor.

2) The name and logo of the organization must be displayed in a conspicuous place visible to the public at the organization's headquarters and branch offices.

### 66. Verification of Existence

1) If an organization fails to provide its report within 3 months from the expiry of the time frame set under this Proclamation for submission of reports, the Justice Bureau shall issue a notice in the gazette to verify its existence.

2) If the organization does indeed maintain existence, the legal representative must be present to explain the situation within 30 days from the publication of the notice Justice Bureau.

3) If the representative does not appear within the period specified in sub-Article 2 of this Article and does not provide sufficient reasons why the organization did not report, the head of the justice office shall submit the case to the Council and decide for the organization to be dissolved;

4) Subject to the provisions referred in sub-Article 1 to 3, any organization related to project implementation must submit a report to the Finance Bureau within the

የገቢውን ምንጭ ያካተቱ መሆን አለባቸው፤

3) ድርጅቱ የሥራ መሪዎች በዚህ አንቀጽ መሠረት የተዘጋጁ የሒሳብ ሰነዶችን፣ የሒሳብ ዓመቱ ካለቀ በኋላ ቢያንስ ለአምስት ዓመት ጠብቀው የማቆየት ግዴታ አለባቸው።

**68. ዓመታዊ የሒሳብ መግለጫና ምርመራ**

1) ማንኛውም ድርጅት ተቀባይነት ባላቸው መመዘኛዎች መሠረት የተዘጋጀ ዓመታዊ የሒሳብ መግለጫ ለፋይናንስ ቢሮ እና ለፍትሕ ቢሮ በአድራሻው መላክ አለበት፤
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም በበጀት አመቱ ከሁለት መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ ድርጅት ገቢን፣ ወጪን፣ ሐብትና ዕዳን የሚያመለክት መግለጫ ብቻ ማቅረብ ይችላል፤
3) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ድርጅት ሒሳብ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ3 ወራት ውስጥ በተመሰከረለት ኦዲተር መመርመር አለበት፤
4) አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት የድርጅቱ አባላት ወይም ለጋሽ ድርጅቶች ወይም ከድርጅቱ ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ያላቸው መንግስታዊ አካላት የሒሳብ ምርመራ እንዲደረግ ከጠየቁ ፋይናንስ ቢሮ እና ፍትሕ ቢሮ የድርጅቱ ሒሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ሊያዙ ይችላሉ።
5) የድርጅቱ ሒሳብ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በአምስት ወራት ውስጥ ካልተመረመረ እና ይህንን ለመፈጸም ድርጀቱ ፈቃደኛ ካልሆነ የፋይናንስ ቢሮ እና ፍትሕ ቢሮ የውጭ ኦዲተር ሾሞ ማስመርመር ይችላሉ፤
6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 መሠረት በፋይናንስ ቢሮ እና በፍትሕ ቢሮ በተሾመው ኦዲተር ለተከናወኑ ማናቸውም የኦዲት ሥራዎች ወጪ የሚከፍለው

time limit set in this decree.

## SECTION FIVE

## ACCOUNTS and ACTIVITY REPORT

### 67. Duty to Keep Accounting Records

1) Any organization shall keep books of account that show the financial transactions in the organization and are prepared in accordance with acceptable accounting standards.
2) The books of account shall contain entries showing all sums of money received and expended by the Organization, the matters in respect of which the receipt and expenditure takes place, name and identity of donors, source of donations; and record of the assets and liabilities of the Organization.
3) The officers of an organization shall preserve any accounting records made for the purposes of this Article for at least 5 years from the end of the financial year of the Organization in which they are made.

### 68. Annual Financial Statement and Audit

1) Any Organization shall submit to the Finance Bureau and Justice Bureau an annual statement of accounts prepared in accordance with acceptable standards.
2) Notwithstanding sub-Article (1) of this Article, Organizations whose annual flow of funds does not exceed Birr 200,000.00, (two hundred thousand) the statement of accounts may choose to only prepare a receipts and payments account and a statement of assets and liabilities.
3) With the exception to the stipulations under Sub-Article (2), all Organizations' account shall be

የሚመለከተው ድርጅት ወይም ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ የሥራ መሪዎቹ ይሆናሉ።

## 69. ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት

1) የሥራ መሪዎች የድርጅቱን የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት ዋና ዋና ክንዋኔዎች የሚያሳይ ሪፖርት የሒሳብ ዓመቱ ሲያልቅ ለፋይናንስ ቢሮ እና ለፍትሕ ቢሮ ማቅረብ አለባቸው፤
2) ማንኛውም የሥራ ክንውን ሪፖርት ለፋይናንስ ቢሮ እና ለፍትሕ ቢሮ ሲቀርብ የሒሳብ መግለጫ አብሮ መያያዝ አለበት፤
3) ፋይናንስ ቢሮ እና ፍትሕ የቀረበላቸዉን ሪፖርት በመመርመር ድርጅቱ ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ማብራሪያ እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል።

## 70. ዓመታዊ ሪፖርት ለሕዝብ ክፍት ስለማድረግ

1) በፍትሕ ቢሮ ተመዝግቦ የሚገኝ ማናቸውም የድርጅት ዓመታዊ ሪፖርት ወይም ሌላ ሰነድ በፋይናንስ ቢሮ፣ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ወይም በድርጅቱ አባላት ሲጠየቅ በማናቸውም አመቺ ጊዜ ክፍት መደረግ አለበት፤
2) ማናቸውም ድርጅት ዓመታዊ የሥራ ክንውን እና የኦዲት ሪፖርቱን ለአባላቱና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ አለበት።

## 71. የባንክ ሒሳብ ስለመክፈት

1) ማንኛውም ድርጅት የባንክ ሒሳብ ለመክፈት በቅድሚያ ከፋይናንስ ቢሮ በጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤
2) ፋይናንስ ቢሮ የባንክ ሒሳብ ለመክፈት ጥያቄ በቀረበለት በ 5 ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፤
3) የማንኛውም ድርጅት የገንዘብ እንቅስቃሴ በስሙ በተከፈተ የባንክ ሒሳብ መከናወን ይኖርበታል፤

examined annually by a Certified Auditor within three months after the end of the financial year.

4) If one third of the organization's members, donors or governmental bodies that have requested the examination of accounts, the Finance Bureau and Justice Bureau may appoint a certified external auditor.
5) Where it appears that the account of an Organization is not audited within five months from the end of that year and the Organization is unshall ing to have it audited, the Finance Bureau and Justice Bureau may appoint a certified external auditor.
6) In accordance with Sub-Article (4) and (5) of this Article, the expenses of any audit carried out by an Auditor appointed by the Finance Bureau and Justice Bureau shall be paid by the Organization concerned, or by its officers if the latter are found to be at fault.

## 69. Annual Activity Report

1) The officers of an organization shall prepare and submit to the Finance Bureau and Justice Bureau every Budget year major activity reports regarding the organization end the Budget year.
2) Every such annual activity report shall have attached to it the annual statement of accounts.
3) After reviewing the reports the Finance Bureau and Justice Bureau may require additional information or explanation.

## 70. Disclosure of Annual Activity Report to the Public

1) Any annual activity report or other document kept by the Justice Bureau, when requested by Finance Bureau or any concerned body or members of the organization, must be made

4) ማንኛውም ባንክ ፋይናንስ ቢሮ ወይም በፍትሕ በተጠየቀ ጊዜ ወዲያውኑ በማናቸውም የድርጅት ሥም የተከፈቱ የባንክ ሂሳቦችን ዝርዝርና የሒሳብ መግለጫዎችን የመስጠት ግዴታ አለበት፤

5) የድርጅት የባንክ ሒሳብ እንቅስቃሴ በመተዳደሪያ ደንቡ በተመለከተው አኳኋን ነው።

## 72. የውጭ ዜጎችን ስለመቅጠር

የሙያ ዘርፉ ልዩ ሙያ የሚጠይቅ እና በሀገር ውስጥ ዜጎች የማይሸፈን ሆኖ ሲገኝ ማናቸውም ድርጅት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሥራ ፈቃድ የተሰጠውን የውጭ ዜጋ መቅጠር ይችላል።

## ክፍል ስድስት

## ሕግን ስለማስከበር

## 73. ምርመራ የማድረግ ሥልጣን

1) ከመንግሥት አካላት፣ ከለጋሽ ድርጅቶች ወይም ከሕዝብ ከሚቀርቡ ጥቆማዎች ወይም ፋይናንስ ቢሮ እና ፍትሕ ቢሮ ሥራቸውን በሚያከናውንበት ወቅት ከሚገኙ መረጃዎች በመነሳት ማናቸውም ድርጅት ሥራውን በሕግ መሠረት እየሰራ ስለመሆኑ ፍትሕ ቢሮ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል፤

2) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም በፍትሕ ቢሮ ምርመራ እንዲደረግ ሲወስን ምርመራውን ለማከናወን በቂ ምክንያት መኖሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ አለበት፤

3) የምርመራ ሥራዎች በተቻለ ፍጥነት በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቁና የድርጅቱን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴና ሕልውና አደጋ ላይ እንዳይጥሉ ፍትሕ ቢሮ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ አለበት፤

open to the public at any given time.

2) All organizations must make available at all times, to their beneficiaries and members, the books of account, audit reports and annual reports.

## 71. Opening a Bank Account

1) An organization shall get a written approval of the Finance Bureau to open a bank account.

2) The Finance Bureau shall respond to requests for such approval within five days from receipt of the request.

3) All financial transactions shall be performed through a bank account opened by an organization in its name.

4) All banks have the obligation to provide the bank statement of accounts held by any organization to the Finance Bureau and Justice Bureau when requested.

5) The Bank Account transaction can be done in the context of the organization rules.

## 72. Employing Foreigners

When the professional field requires special skills and cannot be covered by Ethiopian citizens, any organization can hire a foreigner who has been granted a work permit in accordance with the relevant law.

## SECTION SIX

## LAW ENFORCEMENT

## 73. Power of Inspection

1) Based on informations from government bodies,

4) ፍትሕ ቢሮ የምርመራ ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ከባድ የሕግ ጥሰት መፈጸሙን ሲያረጋግጥና በዚህ ምክንያትም የድርጅቱ እንቅስቃሴ ማገድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በፋይናንስ ቢሮው የሚመለከተው የስራ ክፍል ሃላፊ ድርጅቱ እንዲታገድ ለፍትሕ ቢሮ ሃላፊ ማቅረብ ይችላል፤

5) የፍትሕ ቢሮ ሃላፊ የድርጅቱ መታገድን አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ የዕገዳ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል:: ሆኖም ሃላፊው በሶስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ዕገዳው ቀሪ ይሆናል፤

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የፍትሕ ቢሮ ሃላፊ በሰጠው ዕግድ ላይ ድርጅቱ በ15 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለጉባኤው ማቅረብ ይችላል፤

7) ድርጅቱ በጉባኤው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ ይችላል።

## 74. አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ

1) ፍትሕ ቢሮ ይህን አዋጅ እና ሌሎች ሕጎችን ለሚጥሱ ድርጅቶች ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ይችላል፤

2) የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ በፅሑፍ ሆኖ የተፈጸመውን የሕግ ጥሰት፣ ሊደረግ የሚገባውን ማስተካከያ እና በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መስተካከል እንዳለበት በግልጽ ማሳየት አለበት፤ ለማስተካከያ የሚሰጠው ጊዜ የተፈጸመውን ጉድለት ወይም ጥፋት ክብደትና የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፤

3) ድርጅቱ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ማስተካከያ የማያደርግ ከሆነ ወይም የፈጸመው ጥፋት ከባድ መሆኑን ፍትሕ ቢሮ ሲያምንበት ለድርጅቱ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ

donor organizations, or the public, or information obtained by the Finance Bureau and the Justice Bureau while performing their work, the Justice Bureau may investigate whether any organization is doing its work in accordance with the law;

2) Notwithstanding sub-Article 1, when deciding to conduct an investigation by the Justice Bureau, it must first ensure that there is sufficient reason to conduct the investigation;
3) The Justice Bureau must take appropriate precautionary measures so that investigations are completed as soon as possible and do not endanger the organization's day-to-day activities and existence;
4) When the Justice Bureau confirms that a serious violation of the law has been committed during its investigation and finds it necessary to suspend the activities of the organization, the head of the relevant work department of the Finance Bureau can submit to the head of the Justice Bureau that the organization be suspended;
5) If the head of the justice office finds it necessary to suspend the organization, he can issue a suspension order for a period not exceeding three months. However, if the justice bureau head does not make a decision within three months, the suspension shall seize to exist;
6) The organization can submit its complaint to the Council within 15 days against the suspension given by the head of the justice Bureau in accordance with sub-Article 5;
7) If the organization is dissatisfied with the decision of the Council, it can file an appeal to the High Court within 30 days from the date of the decision.

ይሰጠዋል፤

4) በተሰጠው ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መሠረት ድርጅቱ አሰራሩን የማያስተካክል ከሆነ ድርጅቱ እንዲታገድ የፍትሕ ቢሮ ሃላፊ ሊወስን ይችላል፤

5) ፍትሕ ቢሮ ሃላፊ ውሳኔ በጉባኤው ካልተነሳ ወይም በፍርድ ቤት ካልታገደ በቀር የዕገዳ ውሳኔው በተሰጠ በሦስት ወራት ውስጥ ማስተካከያ ያላደረገ ድርጅት እንዲፈርስ ጉባዔው ሊወስን ይችላል፤

6) በጉባኤው የመፍረስ ውሳኔ የተሰጠበት ድርጅት አባላት፣ መሥራቾች ወይም ኃላፊዎች ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታቸውን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ፤

7) በድርጅቱ የተፈጸመው ሕግ የመተላለፍ ተግባር በወንጀል የሚያስጠይቅ ሲሆን ፍትሕ ቢሮ ጉዳዩን እንዳስፈላጊነቱ ስልጣን ካለው የፖሊስ ተቋም በጋራ ወይም በተናጠል በፖሊስ ተቋም እንዲጣራ ይመራል፡፡

8) ፋይናንስ ቢሮ ይህን አዋጅ ተከትሎ በፕሮጀክት ትግበራ አሰራር ላይ በሚጥሱ ድርጅቶች ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ይችላል፤

## 75. የመሰማት መብት

በማንኛውም ድርጅት ላይ የትኛውንም ዓይነት አስተዳደራዊ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ድርጅቱ መከራከሪያዎቹንና ማስረጃዎቹን የማቅረብና የመሰማት መብት አለው፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለ ድርጅቶች መዋሐድ፣ መከፋፈል እና መለወጥ

## 74. Administrative Measures

1) The Justice Bureau may give warning to organizations that do not comply with this proclamation or other laws.

2) The warning must be in writing and shall specify the violation, the measures to be taken and the time frame to rectify the violation. Such time frame shall take into account the gravity of the violation and the complexity of the case.

3) If the fault committed by the organization is grave or the organization fails to redress its fault after being given clear warning, the Justice Burea shall give the organization a strict warning.

4) The Justice Burea Head may order the suspension of the organization if the organization fails to alter or rectify its practice after receiving a strict warning.

5) The Council shall decide that an organization which failed to make the necessary rectifications within three months following the suspension order shall be dissolved unless the Justice Head's suspension order has been lifted by the Council or is blocked by court order.

6) The Members, Founders or Managers of the Organization that is dissolved by the decision of the Council can appeal to Regional High court with in 30 days following the decision.

7) The violation of the law committed by the organization is a criminal offense and the Justice Bureau shall direct the case to be investigated jointly or separately by the police institution as necessary.

8) The Finance Bureau may issue warnings to organizations that violate project implementation procedures following this proclamation;

**76. መዋሐድ**

1) ቁጥራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ድርጅቶች አግባብነት ባላቸው ሕጎችና በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት በአዲስ ስም ወይም ከሚዋሐዱት ድርጅቶች በአንዱ ስም ሊዋሐዱ ይችላሉ፤
2) ውሕደቱ ሲፈጸም የቀድሞዎቹ ድርጅቶች መብትና ግዴታዎች እንዲሁም በውስጣቸው የነበሩ ሰራተኞች እንደአግባብነታቸው በውህደት ወደተፈጠረው ድርጅት ይተላለፋሉ፤
3) በውሕደቱ የተፈጠረው አዲስ ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት መመዝገብ አለበት።

**77. መከፋፈል**

1) አንድ ድርጅት በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተመለከተው መሠረት በድርጅቱ የበላይ አካል ውሳኔ ሊከፋፈል ይችላል፤
2) በመከፋፈሉ ውሳኔ ላይ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በቀር በክፍፍሉ የተፈጠረው እያንዳንዱ ድርጅት የቀድሞው ድርጅት ላለበት ግዴታና መብት እኩል ተካፋይ ነው፤
3) የቀድሞው ድርጅት ህልውና የሚያበቃው ለአዲሶቹ ድርጅቶች የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሲሰጥ ነው፤
4) በአዲሶቹ ድርጅቶች ሙሉ ስምምነት ከነሱ አንዱ የቀድሞውን ድርጅት ስም ይዞ ሊቆይ ይችላል።

**78. መለወጥ**

1) አንድ ድርጅት በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተመለከተው መሠረት በድርጅቱ የበላይ አካል ውሳኔ ወደሌላ ዓይነት ድርጅት ሊለወጥ ይችላል።
2) ለውጡ ሲፈጸም የቀድሞው ድርጅት መብትና ግዴታዎች

**75.The Right to be Heard**

Before any administrative measures taken by any organization, it has the right to be heard and present its arguments and evidences.

## SECTION SEVEN

## MERGER, DIVISION AND CONVERSION OF ORGANIZATIONS

**76. Merger**

1) Two or more organizations may merge into one under a new name or under the name of one of the organizations in accordance with relevant laws and in accordance with their rules.
2) The rights and obligations of the former organizations and based on their relevancy the Employees of those organizations shall be transferred to the newly formed organization.
3) The newly established organization shall be registered in accordance with this Proclamation.

**77. Division**

1) An organization may be divided into two or more organizations upon the decision of its supreme organ in accordance with its rules.
2) Unless stated otherwise in the decision to divide the organization, the organizations that result from the division shall bear the obligations and utilize the rights equally.
3) The existence of the former organization shall cease

እንዲሁም በውስጣቸው የነበሩ ሰራተኞች እንደአግባብነታቸው ወደተለወጠው ድርጅት ይተላለፋሉ።

3) የተለወጠው አዲስ ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና መመዝገብ አለበት።

## ክፍል ስምንት

## ስለድርጅቶች መፍረስ

### 79. የድርጅቶች መፍረስ

1) አንድ ድርጅት የሚፈርሰው፡-

ሀ/ በመተዳደሪያ ደንቡ ሥልጣን ባለው አካል እንዲፈርስ ሲወሰን፣

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 66 ንዑስ አንቀጽ 3 ወይም አንቀጽ 76 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ድርጅቱ እንዲፈርስ በጉባኤው ሲወሰን፤ ወይም

ሐ/ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ነው፤

2) ፍርድ ቤት አንድ ድርጅት እንዲፈርስ የሚወስነው፡-

ሀ/ ድርጅቱ በከባድ የወንጀል ድርጊት ወይም በተደጋጋሚ በቀላል ወንጀል በመሳተፍ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም

ለ/ ዕዳውን የመክፈል ችሎታ የሌለው ሲሆን ብቻ ነው፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) መሠረት በአባላት ውሳኔ የፈረሰ ድርጅት ውሳኔውን ለፍትሕ ቢሮ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ 3 መሠረት ድርጅቱ ለፍትሕ ቢሮ ከሚያቀርበው ማስታወቂያ ጋር ድርጅቱ እንዲፈርስ የተወሰነበትን ቃለ ጉባኤ፣ የድርጅቱን ወቅታዊ የሥራ ክንውንና የሒሳብ መግለጫ አያይዞ ማቅረብ አለበት።

at the time when the certificates of registration are issued to the new organizations.

4) With the unanimous consent of all newly formed organizations, one of the newly formed organizations may retain the name of the previous organization.

### 78. Conversion

1) Any organization may be converted into another form of organization where its supreme organ so decides in accordance with its rules.

2) The rights and obligations of the former organization and based on their relevancy the servants of those organizations shall be transferred to the organization after the conversion.

3) The converted organization shall be registered again in accordance with this Proclamation.

## SECTION EIGTH

## DISSOLUTION OF ORGANIZATIONS

### 79. Dissolution

1) An organization may only be dissolved:

a/ upon the decision of the Organization's competent organ in accordance with its rules;

b/ When the Council decides that the organization shall be dissolved in accordance with Article 66(3) or 74(5) of this Proclamation;

## 80. የመፍረስ ውጤት

1) በአንቀጽ 81 መሠረት ድርጅቱ እንዲፈርስ ሲወሰን ንብረቱ ወዲያውኑ በፋይናንስ ቢሮ እና በፍትሕ ቢሮ በሚሾም ሒሳብ አጣሪ ኃላፊነት ሥር ይሆናል፤

2) ሒሳብ አጣሪው ከድርጅቱ ዓላማ ጋር የተያያዙና ሊቋረጡ የማይችሉ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ካልሆነ በስተቀር ከሒሳብ ማጣራት ውጪ ሌላ ተግባር ማከናወን አይችልም፤

3) የድርጅቱን ዕዳዎችና የማፍረስ ሂደቱን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወጪዎች ተጠናቀው ከተከፈሉ በኋላ ሒሳብ አጣሪው የድርጅቱ ቀሪ ገንዘብ ወይም ንብረት በድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ ወይም በድርጅቱ የበላይ አካል አስቀድሞ በተወሰነው መሠረት ለሌላ ድርጅት እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ ወይም በድርጅቱ የበላይ አካል ውሳኔ ላይ ካልተመለከተ ቀሪ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ፍትሕ ቢሮ በሚወስነው መሠረት ፋይናንስ ቢሮ ለሌላ ድርጅት እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

5) የድርጅቱ የሒሳብ ማጣራት ሥራዎች ሲጠናቀቁ በሒሳብ አጣሪው ጠያቂነት ፍትሕ ቢሮ ድርጅቱን ከመዝገብ ይሰርዛል፤

6) የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ህብረቶች ወይም የህብረቶች ህብረት በሚፈርሱበት ጊዜ ቀሪ ንብረቶች ወደ አባል ድርጅቶች ወይም ህብረቶች ሊተላለፉ ይችላሉ፡፡

## 81. በኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ስለመጠቀም

c/ By the decision of Regiona High Court.

2) A court can dissolve an organization only when;

a/ It is convicted of a serious criminal offence or is repeatedly found guilty of a minor criminal offence; or

b/ The organization is insolvent.

3) An organization dissolved in accordance with sub Article 1(a) of this Article shall notify the decision to Justice Bureau within fifteen days.

4) The notification submitted to the Justice Bureau under sub Article 3 shall be accompanied with the resolution to dissolve the organization, the current activity report and statement of account of the organization.

## 82. Effects of Dissolution

1) According to Article 81 once the dissolution of an organization is ordered, the property of the organization shall forthwith vest in the liquidator appointed by the Finance Bureau and Justice Bureau.

2) The liquidator shall not perform any activities other than those necessary for its liquidation unless such activities are within the object of the organization and cannot be interrupted.

3) Once the debts of the organization are paid and the costs of dissolution are settled, the liquidator shall affect the transfer of the remaining money or property to another organization in accordance with the Rules or a prior decision of the supreme body of the organization.

4) If the rules or the decision of the Organization's supreme body do not provide for a recipient organization as per sub Article 3 of this Article, the remaining money or property shall be transferred to another organization by Finance

በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው ደንብ መሠረት የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ይበልጥ ዘመናዊ፣ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የኤሌክትሮኒክ ዘዴዎችን በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

**ክፍል ዘጠኝ**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

## 82. የድርጅቶች ምክር ቤት

1) በክልል ደረጃ በሁሉም ድርጅቶች ሙሉ ተሳትፎ የሚመራ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) ፋይናንስ ቢሮ ከፍትሕ ቢሮ ጋር በመተባበር የምክር ቤቱን መሥራች ጉባዔ ይጠራል፤ ያስተባብራል፤

3) ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ፣ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ አደረጃጀቶች ይኖሩታል፣ ምክር ቤቱ የራሱን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፤

4) ድርጅቶች በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ የሚወከሉበት ስርዓት በምክር ቤቱ መመሪያ ይወሰናል፤

5) ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ከፋይናንስ ቢሮ፣ ከፍትሕ ቢሮ፣ ከለጋሾችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ዘርፉ ሊከተለው የሚገባውን የስነ-ምግባር ደንብና ማስፈጸሚያ ስልት ያወጣል፤ አተገባበሩን በቅርበት ይከታተላል፤

ለ/ በድርጅቶች ምዝገባና አስተዳደር ላይ ለፋይናንስ ቢሮ፤

Bureau according to decision of the Justice Bureau.

5) After the liquidation process is concluded, the Justice Bureau shall cancel the name of the organization from its registry upon the request of liquidator.

6) without prejudice to the provisions of this Article when Consortiums or consortium of consortiums are Dissolved, the remainning properties may be transferd to the member organizations or Consertiums.

## 81.The use of electronic means

In accordance with this proclamation and the regulations issued following this proclamation, electronic methods shall be widely used to make the service delivery system of the sector more modern, efficient and effective.

**SECTION NINE**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

## 82. Council of Civil Society Organizations

1) A Council of Civil Society Organizations governed by the full participation of all civil society organizations within region has been duly established by this Proclamation.

2) The Bereau of Finance in collaboration with Justice Bureau shall convene and coordinate the founding meeting of the Council.

3) The Council of Civil Society Organizations shall have a General Council, Executive committee and other necessary structures essential for the work. The council shall enact its own internal rules.

4) The procedures for representation of

ለፍትሕ ቢሮና ለጉባዔው ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል፤

ሐ/ ዘርፉን ይወክላል፤ያስተባብራል፤

6) ምክር ቤቱ በጉባኤው ውስጥ ድርጅቶችን የሚወክሉ ተወካዮችን ይመርጣል፤

7) የምክር ቤቱ በጀት ከአባላት መዋጮና ከሌሎች ሕጋዊ ምንጮች ይሆናል፤

8) ለምክር ቤቱ መመሥረትና መጠናከር የፍትሕ ቢሮ እና የፋይናንስ ቢሮ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን ትብብርና ድጋፍ ያደርጋሉ።

**83. የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ**

1) በክልሉ ፋይናንስ ቢሮ የሚተዳደር የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የሲቪል ማህበረብ ፈንድ በጎ ፈቃደኝነትን እና የዘርፉን ዕድገት ለማበረታታት፣ በተለይም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች የሚያገለግሉ ድርጅቶችን ለማበረታታት ይውላል፤

3) የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ ገቢውን የሚያገኘው፡-

ሀ/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ከፈረሱ ማህበራትና ድርጅቶች የተሰበሰበ ሀብት ወይም ንብረት ካለ፣

ለ/ በፍትሕ ቢሮ ወይም ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሚፈርሱ ድርጅቶች የሚገኝ ንብረት፣

ሐ/ በመንግሥት ለፈንዱ የሚደረግ ድጎማ፤

4) ድርጅቶች ለሲቪል ማህበረሰብ ፈንዱ መዋጮ ማድረግ

organizations in the General Council shall be determined by the Directives of the Council of Civil Society Organizations.

5) The Council of Civil Society Organizations shall have the following powers and functions;

a/ Enact the Code of Conduct for the sector, and devise enforcement mechanisms in consultation with the Finance Bureau and Justice Bureau, donors and other stake holders; follow up the implementations.

b/ Shall advise the Finance Bureau, Justice Bureau and Council on the registration and administration of the organizations,

c/ Represent and coordinate the civil society sector.

6) The council shall select members of the Council that shall represent organizations.

7) The source of the council‟s budget shall be from member‟s contribution and other legal sources.

8) The Justice Bureau, Finance Bureau in cooperation with other stake holders shall extend the necessary cooperation for establishment and strengthening of the council.

**83. Civil Society Fund**

1) A civil society fund administered by the Finance Bureau is hereby established.

2) The civil society fund shall be used to encourage volunteerism and development in the sector, and provide incentives to organizations working with vulnerable groups.

አይችሉም።

5) የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ ፋይናንስ ቢሮ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል ።

**84. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

በዚህ አዋጅ ከተደነገጉ ጉዳዮች ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ልማድ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**85. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1) ከዚህ አዋጅ በፊት የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን መሠረታዊውን መብቶችና ግዴታዎች እስካልተቃረኑ ድረስ ባሉበት ይቀጥላሉ፤

2) ከዚህ በፊት በክልሉ የተመዘገቡ ማኅበራት ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደገና በክልሉ ፍትሕ ቢሮ መመዝገብ አለባቸው።

**86. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤

2) ፋይናንስ ቢሮ እና ፍትሕ ቢሮ በዚህ አዋጅ የተሰጣቸዉን ሥላጣንና ተግባራት እንዲሁም በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት የሚወጣዉን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጡ ይችላሉ።

**87. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ከፀደቀበት ከመጋቢት 5 ቀን 2016 ዓ/ም ጀምሮ የፀና

3) The Civil Society Fund collects income from:

a/ Resource or properties obtained from charities and societies dissolved before the enactment of this proclamation, if any;

b/ properties obtained from organizations dissolved by the decision of Justice Bureau or Court;

c/ Subsidy from the Government to the Fund.

4) Organizations can not contribute to civil society fund.

5) The Finance Bureau can issue Directives on the administration of the civil society fund.

**84. Repealed And Unenforceable Laws**

Any law, regulation, directive, custom or practice inconsistent with the matters provided for in this proclamation shall have no effect.

**85. Transitional provisions**

1) The rights and duties that existed before this proclamation shall continue to exist as long as they do not contradict with the basic rights and duties set forth in this proclamation;

2) Organizations previously registered in the region must be re-registered in the region's Justice Bureau within one year from the effective date of this proclamation.

**86. Authority to issue rules and regulations**

1) The Regional Administrative Council may

| | |
|---|---|
| ይሆናል። | issue regulations to implement this proclamation;<br>2) The Finance Bureau and the Justice Bureau may issue directive necessary to enforce the powers and duties given by this proclamation as well as the regulations issued by the Regional Administrative Council. |
| **አርባምንጭ**<br>**መጋቢት 5 ቀን 2016 ዓ.ም**<br>**ጥላሁን ከበደ**<br>**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር** | **87. Effective Date**<br><br>This Proclamation shall be effective from March 14, 2024 when it was approved by the Southern Ethiopian Regional Government Council.<br><br>**Done at Arbaminch**<br>**March 14, 2024**<br>**Tilahun Kebede**<br>**President of South Ethiopia Regional State** |